# የስሚ ስሚ ማስረጃ (HEARSAY EVIDENCE)

በተስፋዬ አባተ አበበ ♣

## አጽህሮተ ይዘት (Abstract)

የስሚ ስሚ ማስረጃ ስለ አንድ ኩነት እውነትነት ችሎት ያልቀረበ ሰው የገለፀውን ሌላው ሰው ችሎት በመቅረብ የሚሰጠው የምስክርነት ማስረጃ ነው፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ በ'ኮመን ሎው' እና በ'ሲቪል ሎው' ምን ያህል ቅቡልነት እንዳለው ይህ ጽሁፍ ይመረምራል፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ በኢትዮጵያ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ጥያቄ የዚህ ጽሁፍ ጭብጥ ነው፡፡ ንጽጽራዊ የጥናት ዘዴን በመጠቀም የ'ኮመን ሎው' እና 'ሲቪል ሎው' ሕጎችና ተሞክሮዎች ተጢነዋል፡፡ ስለ ጭብጡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት፣ በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ እና በወ/ሥ/ሥ/ሕግ፣ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት ተመርምረዋል፤ በተለያዩ ጊዜያት በፍ/ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችም ተዳስሰዋል፡፡ የስሚ ስሚ በኢትዮጵያ ቅቡልነት አለው ወይስ የለውም ለሚለው ጭብጥ በሚሰጡ ሁለት አስተያየቶች ላይ ትንተና ቀርቧል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገመንግሥት አንቀጽ 20(4) መሠረት የወንጀል ተከሳሾች የቀረቡባቸውን ማስረጃዎች የመጋፈጥ መብት ያላቸው በመሆኑና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲም ይህንኑ ስለሚያጠናክር የስሚ ስሚ ማስረጃ በመርህ ደረጃ (in principle) ተቀባይነት እንዳይኖረውና በግልፅ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) ብቻ ቅቡል እንዲሆን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ፀሀፊው ያምናል፡፡

## ቁልፍ ቃላት (Key words)

የስሚ ስሚ ማስረጃ፣ የባለሙያ ማስረጃ፣ አካባቢያዊ ማስረጃ፣ የስሚ ስሚ ደንብ፣ የስሚስሚ ማስረጃ በኢትዮጵያ

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v6i1.4

## መግቢያ

በ"ኮመን ሎው" እና በ"ሲቪል ሎው" የሕግ ሥርዓቶች ስለ ስሚ ስሚ ማስረጃ የተለያዩ አቋሞች አሉ፡፡ በሀገራችንም ይህን ጉዳይ በተመለከተ የሕግ ባለሙያዎች የተለያዩ አቋሞች ይይዛሉ፡፡ በመርህ ደረጃ አንድ ማስረጃ ቅቡልነት የሚኖረው በምርመራ ላይ ላለው ኩነት (fact) አግባብነት እንዲሁም በማስረጃነት ለመቅረብ ብቃት ሲኖረው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የማስረጃ ቅቡልነት ማለት ማስረጃው ኩነትን ለማስረዳት አግባብነት ያለው ከመሆን በተጨማሪ ሕግ እንዳይቀርብ ያልከለከለው መሆን አለበት፡፡[1] በ'ኮመን ሎው' የትኞቹ ማስረጃዎች ቅቡልነት እንዳላቸው የማስረጃ ሕጉ በዝርዝር ስለሚያስቀምጥ የማስረጃ ቅቡልነት በሕግ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ማናቸውም አግባብነት ያለው ማስረጃ ቅቡልነት ያለው ሲሆን በአንፃሩ ለኩነቱ አግባብነት

---

♣ ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ም (አ.አ.ዩ)፣ LL.D Candidate፣ ረዳት ፕሮፌሰር፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፣ የሕግ አማካሪና በፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት ጠበቃ፡፡ ለዚህ ጽሁፍ ይዘትና ቅርጽ መዳበር የሚዛን አርታዒያን እንዲሁም ማንነታቸውን ያላወቅኋቸው ሁለት ገምጋሚዎች (ሪቪወሮች) የሰጧቸው አስተያየቶች በእጅጉ የጠቀሙኝ ስለሆነ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

Email <testigph@gmail.com>

[1] Justice Alfredo L. Benipayo, (2004), "Evedence: Basic Principles and Selected Problems" *US Law Review*, Vol. XLVIII, p. 94.

የሌለው ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም አንድ ማስረጃ ቅቡልነት እንዲኖረው ለኩነቱ አግባብነት ሊኖረው ይገባል፡፡[2]

አግባብነት የሚባለው ተጠይቃዊ (logical) በሆነ ሁኔታ አንድን ኩነት ለማረጋገጥ ወይም ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ዝንባሌ ሲሆን ስለአንድ ኩነት አንድ ድማዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል የማሳመን ብቃት ነው፡፡[3] አግባብነት ያለው ማስረጃ ማለት አንድን ኩነት ለማረጋገጥ የሚያስችልና ዳኛ ወደ አንድ ድምዳሜ እንዲደርስ የሚረዳ ማስረጃ[4] ማለት ነው፡፡[5] በ'ኮመን ሎው' አግባብነት ያለው ማስረጃ ቅቡል እንዲሆን በማስረጃ ደንብ (Rules of Evidence) ያልተከለከለ መሆን አለበት፡፡[6] በመሆኑም በ'ኮመን ሎው' የማስረጃ ሕግ ስለ ማስረጃ አግባብነትና ቅቡልነት በዝርዝር ስለሚደነግግ ዳኛው የአንድን ማስረጃ አግባብነተና ቅቡልነት በማስረጃ ሕጉ መሠረት ይወስናል፡፡ የስሚ ስሚም በዚሁ የማስረጃ ሕግ የሚገዛ ነው፡፡ በ'ሲቪል ሎው' ግን ከዚህ በተለየ መልኩ የማስረጃን አግባብነትና ቅቡልነት በሚመለከት በዝርዝር በሕግ ያልተደነገገ ስለሆነ የማስረጃን ተቀባይነት የሚወስነው ዳኛው ነው፡፡[7]

በኢትዮጵያ ስለስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት የተለያዩ አቋሞች ያሉ ሲሆን የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማም ስለ ስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት በተለያዩ የሕግ ሥርዓቶች ያሉትን አቋሞች ወይም መርሆዎች በመመርመር በሀገራችን ሊያዝ የሚገባው አቋም ምን መምሰል እንዳለበት አስተያየት መሰንዘር ነው፡፡ ስለ ጽንሰ ሀሳቡ የተሻለ ግንዛቤን መጨበጥ ይቻል ዘንድ ስለ ትርጓሜውና ባህርይ፣ ከምስክርነት ማስረጃ ጋር ስላለው ዝምድና፣ ከአካባቢያዊ ማስረጃ ጋር ስላለው ግንኙነት፣ እንዲሁም ከባለሙያ ማስረጃ ጋር ስላለው ልዩነትና አንድነት ከተመለከትን በኋላ በ'ኮመን ሎው' እና በ'ሲቪል ሎው' ስለ ስሚ ስሚ ማስረጃ ያሉትን ደንቦች እንመረምራለን፡፡ በመጨረሻም የስሚ ስሚ ማስረጃ በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ለመመርመር በሀገራችን በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎች እንመለከታለን፡፡

## 1. የስሚ ስሚ ማስረጃ ምንነት

በዚህ ክፍል ውስጥ መጀመሪያ ስለ ስሚ ስሚ ማስረጃ ምንነት፤ እንዲሁም የስሚ ስሚ ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ስላለው ግንኙነት ምልከታ እናደርጋለን፡፡

---

[2] See generally Rymond N. Emson, (2006), *Law of Evidence*, (Palgrave Macmillan Law Masters).

[3] Bryan A. Garner, (2004), *Blacks' Law Dictionary*, (8th Edition), (West & Thomas Business), p. 1316.

[4] ‹‹ማስረጃ›› /Evidence/ ተሟጓቾች በአቤቱታቸው አማካኝነት ለፍርድ ቤት ያስያዙትን ጭብጥ የሚያረጋግጡበት ዘዴ ነው፡፡ Sideney Philipson (1963), *Philipson on Evidence, p.* 2. በሌላ አነጋገር "ማስረጃ" ማለት በአንድ የክርክር ጉዳይ ላይ ተሟጋቾች ጥያቄያቸው አግባብና እውነት መሆኑን በምስክሮች፣ በሠነድ ወ.ዘ.ተ. ለፍርድ ቤቱ ወይም ዳኝነት ለሚሰጠው አካል የሚያረጋግጡበት አሊያም ውድቅ የሚደርጉበት ዘዴ ነው፡፡ Henery Campbell Black (1968), *Black's Law Dictionary* (4th Rev.ed), p. 656፡፡ ከነዚህ ትርጓሜዎች እንደምንረዳው "ማስረጃ" የሚለው ቃል አንድን ጭብጥ ለማረጋገጥ አሊያም ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ማናቸውም ዓይነት የማረጋገጫ ዘዴ ነው፡፡

[5] See Emson, *supra* note 2.

[6] Benipayo, *supra* note 1, p. 94.

[7] ይህን አስመልክቶ የሕግ ምሁራን እንዳስቀመጡት የማስረጃ ጉዳይ ለፈራጅ ህሊና የተተወ ነው ፡፡(በሲቪል ሎው፤ ዮሐንስ ሕሩይ፣ በታጠቅ ታደሰ ለተዘጋጀው የኢትዮጵያ የማስረጃ ሕግ መሠረተ ሐሳቦች የመቅድም መቅድም፣ 1996 ዓ.ም. ገጽ I ፡፡) ሆኖም ግን በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ እንዲሁም በሕገ-ወጥ መንገድ የተሰበሰበ ማስረጃ ለኩነቱ አግባብነት ቢኖረውም እንኳ ቅቡልነት ሌለው ስነመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገመንግሥት አንቀጽ 19(5) እና በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ 3.16.1 ተቀምጧል፡፡

## 1.1. የስሚ ስሚ ማስረጃ ትርጉም

የስሚ ስሚ ማስረጃ አንዱ የማስረጃ ዓይነት ነው፡፡ በ'ኮመን ሎው' የሕግ ሥርዓት ትርጓሜ መሠረት "የስሚ ስሚ ማስረጃ" ማለት ፍርድ ቤት ችሎት ካልቀረበ ሰው በምርመራ ላይ ስላለው ኩነት (fact) እውነተነት ወይም ሀሰተነት ያገኘውን ሌላ ሰው ፍርድ ቤት በመቅረብ በቃል፣ በጽሁፍ አሊያም ቃል አልባ በሆነ ድርጊት (non-verbal conduct) የሚሰጠው ማረጋገጫ ነው፡፡[8]

የስሚስሚ በምርመራ ላይ ስላለው ኩነት በቀጥታ ያልሰማ፣ ያላየ፣ ያላሸተተ፣ ወይም ያላወቀ ሰው ለፍርድ ቤት የሚያቀርበው ነው፡፡ የስሚ ስሚ ማለት አንድን ኩነት ለማረጋገጥ ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጠ መግለጫ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ትርጓሜ ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጠ መግለጫ ማለት ምን ማለት ነው? በፍርድ ቤት የተያዘውን ጉዳይ ዕውነተነት ለማረጋገጥ ነውን የተሰጠው? የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡[9]

አንዳንድ ዘመናዊ የማስረጃ ሕግ ኮዶች በተለይም ደግሞ የአሜሪካ የፌደራል የማስረጃ ደንብ እና የካሊፎርኒያ የማስረጃ ኮድ የስሚ ስሚ ማስረጃን ከላይ ከተገለፀው ጠበብ ባለ ሁኔታ ይተረጉሙታል፡፡ ለምሳሌ፤ የአሜሪካ ፌደራል ማስረጃ ደንብ በቁጥር 801 ሥር የስሚ ስሚ ማስረጃ፡-

1. ያልተረጋገጠ የድርጊት መገለጫን (non-assertive conduct),
2. ምስክሩ በሌላ ቦታ ቀደም ሲል የሰጣቸው የተለያዩ መግለጫዎችን፣
3. በባለጋራ የተሰጡ የእምነት ቃላትን እና
4. በወንጀል ተካፋዮች (conspirators) የሚሰጡ መግለጫዎችን

እንደማያካትት ተደንግጓል፡፡[10]

ሮጀር እና ጆን በበኩላቸው የስሚ ስሚ ማስረጃን ሲተረጉሙት 'ፍርድ ቤት ችሎት ያልቀረበ ሰው[11] ስለ አንድ ኩነት እውነተነት የገለፀውን ሌላው ሰው ፍርድ ቤት በመቅረብ የሚሰጠው ማስረጃ ነው'[12] ብለውታል፡፡ ከዚህ ትርጓሜ እንደምንገነዘበው የስሚ ስሚ ማስረጃ ሦስት ነጥቦችን ማሟላት ይገባዋል፡፡

---

[8] John, R. Walts, (*1997), Introduction to Criminal Evidence* (Fourth Edition), P.73; In the 1995 Civil Act of English, hearsay is defined as 'a statement made otherwise than by a person while giving oral evidence in the proceedings which is tendered as evidence of the matters stated'. In a criminal case, it is defined as 'a statement not made in oral evidence in the proceedings [which is tendered] as evidence of any matter stated'. See Raymond, *supra* note 2, p.139.

[9] Ming –woei Chang, (October 2006), "Adoption of the Common Law Hearsay Rule in a Civil Law Jurisdiction: a Comparative Study of the Hearsay Rule in Taiwan and the United States" *Electronic Journal of Comparative Law*, Vol. 10.2available at <http://www.ejcl.org> Accessed on 13/07/ 2012, pp. 18-9.

[10] Walts, *supra* note 8.

[11] ፍ/ቤት ያልቀረበ ሰው ተናጋሪ -declarant - ይባላል፡፡ Declarant is a person who makes a statement. See Rule 801 of Ohio Rules of Evidence, Effective as of July 1, 1980 and amended on July 1, 2007.

[12] Hydoc Roger and Sonsteng John, (1995), *Evidence, Objections and Exhibits* (West Publishing Co), p. 77.

1. በመጀመሪያ ስለ አንድ ኩነት የሚሰጥ መግለጫ[13] ሊኖር ይገባል፤
2. መግለጫው በጽሁፍ፣ በቃል አሊያም በድርጊት ሊሰጥ ይችላል፤
3. የስሚ ስሚ ማስረጃ ፍርድ ቤት ባልቀረበ ሰው ከፍርድ ቤት ውጭ የሚገለጽና በሌላ ሰው ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማስረጃ ነው፡፡

እዚህ ላይ ስለአንድ ሁኔታ የሚሰጥ መግለጫ የስሚ ስሚ ማስረጃ መሆን አለመሆኑ መጤን አለበት፡፡

> ለምሳሌ፣ ከበደ "ሚችን በጥይት ደረቱ ላይ የመታው አበበ ነው" ሲል ሰማሁት የሚለው መግለጫ የስሚ ስሚ ሲሆን "ሚች በጥይት ደረቱ ላይ ተመትቶ አየሁት" የሚለው መግለጫ ግን ሁነትን፣ ድርጊትን የሚገልፅ በመሆኑ የስሚ ስሚ ማስረጃ አይደለም፡፡

ፕሮፌሰር ሮጀር ሲ. ፓረክ እንደጻፉት ሁለት ዓይነት የስሚ ስሚ ትርጓሜዎች አሉ፡፡ እነርሱም፣ ንግግር ተኮር (assertion centered) ወይም ተናጋሪ ተኮር (declarant centered) ናቸው፡፡ በንግግር ተኮር ትርጓሜ መሠረት አንድ መግለጫ የአንድን ኩነት እውነትነት ለማረጋገጥ ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጠ ከሆነ የስሚ ስሚ ነው፡፡ በተናጋሪ ተኮር ትርጉም መሠረት ደግሞ መግለጫው በተናጋሪው ማንነትና ተዓማኒነት ላይ የተመሠረተ ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጠ መግለጫ ነው፡፡[14]

የስሚ ስሚ ዋና ሀሳብ ማስረጃ የመጋፈጥን መብት የሚመለከት ቢሆንም ከክራውፎርድ ጉዳይ (*Crawford v. Washington)* በኋላ ግን ንግግር ተኮርና ተናጋሪ ተኮር አተረጓጎሞችን ማጣመር ያሻል የሚል አመለካከት አለ፡፡ ንግግር ተኮር አተረጓጎም እውነትን ፍለጋ ሲያገለግል፣ ተናጋሪ ተኮር ደግሞ የተናጋሪውን እውነት ተናጋሪነት፣ የመተረክ ችሎታ፣ የማስታወስና የመገንዘብ ችሎታ ለመፈተን ያገለግላል፡፡ በመሆኑም እውነትን ከማረጋገጥ ውጭ የሆኑ ጉዳዮች ከሆኑ ከፍ/ቤት ውጭ የተሰጡ መግለጫዎች መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ሳያስፈልግ ቅቡልነት ይኖራቸዋል፡፡[15]

በጥቅሉ "የስሚ ስሚ ማስረጃ በወሬ ወሬ እንዲህ ሲባል ሰማሁ ወይም እገሌ እንዲህ ሲል ነገረኝ"[16] በማለት ሰዎች የሚሰጡትን መረጃ ያጠቃልላል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የስሚ ስሚ ማስረጃ የቃል፣ የጽሁፍ፣ ወይም የድርጊት ሊሆን ይችላል፡፡

---

[13] መግለጫ በእንግሊዝኛ "statement" የሚለውን ቃል የሚተካ ሲሆን Statement is 1) an oral or written assertion or 2) nonverbal conduct of a person, it is intended by the person as an assertion. See Rule 801 of Ohio Rules of Evidence, *ibid.*

[14] Chang, *supra* note 9, p. 20.

[15] *Ibid.*

*See* also *Crawford v. Washington*, The Supreme Court ruled that witnesses must appear in court for cross examination so as to ensure the right to confrontation. (Rebecca Sims Talbott, October 2010, "What remains of the "Forfeited" Right to Confrontation? Restoring Six Amendment Values to the Forfeiture-by-Washington Rule in light of Crawford v. Washington, 541 U.S. 36 (2004); and Giles v. California", New York University Law Review, vol. 85, p. 1291)

[16] ታደለ አጥናፉ፣ (1981)፣ ስለ ማስረጃ ህግ መግቢያ ለአውራጃ ዐቃብያነ ሕግ ማስተማሪያ የተዘጋጀ፣ ፍትህ ሚኒስቴር (ያልታተመ)፣ ገጽ 35

## 1.2. የስሚ ስሚ ማስረጃና የምስክርነት ማስረጃ ዝምድናና ልዩነት

የምስክርነት ማስረጃ አንድ ሰው ስለ አንድ ኩነት ለፍትህ አካላት በቃሉ የሚሰጠው ማረጋገጫ ሲሆን፣ ይህም የአንድን ኩነት መኖር፣ አለመኖር አሊያም እውነት መሆን አለመሆኑን የምናረጋግጥበት አንዱ ዘዴ ነው፡፡ የሕግ ምሁራን እንደሚሉት የምስክርነት ማስረጃ (የማስረዳት ብቃት እስካለው ድረስ) ያለሠነድ ማስረጃ ብቻውን አንድን ኩነት ለማስረዳት ይችላል፡፡[17] አንድን ፍሬ ነገር በምስክርነት ማስረጃ ማስረዳት ይቻላል ሲባል ግን ማስረጃው በምስክሮች አፍ የግድ መነገር አለበት ማለት አይደለም፣ ምስክሩ ሀሳቡን ለመግለጽ እስከቻለ ድረስ በአፉ ከመናገር ይልቅ ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀሙ የግድ ከሆነ በ"ኮመን ሎው" የሕግ ሥርዓት ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ሊቀበለው ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት ምስክሩ መናገር የተሳነው ከሆነ የምስክርነት ማስረጃውን በምልክት ወይም በጽሁፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡[18]

‹‹ምስክር›› ማለት በአካል ከሥፍራው በመገኘት ስለአንድ ጉዳይ የተመለከተ፣ ያስተዋለ ሰው ነው፡፡ በዓይኑ ስለተመለከተው፣ በጆሮው ስለሰማው፣ በእጁ ስለዳሰሰው፣ በምላሱ ስለቀመሰው ወይም በአፍንጫው ስላሸተተው ኩነት ለፍትህ አካላት (ለፍርድ ቤት) የሚያስረዳ ሰው ምስክር ይባላል፡፡[19] ምስክሮች ስለ አንድ ጉዳይ የሚመሰክሩት ያዩትን፣ የሰሙትን ወ.ዘ.ተ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ጎረቤቱ የሆኑት ባልና ሚስት ሲጣሉና ሲጨቃጨቁ ይሰማል፣ በጠብመንጃም ባል ሚስትን ሲገድል ይመለከታል፡፡ ይህ ደረጃ የመገንዘብ ደረጃ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ውሎ ማደር ይኖራል፡፡ ይህ ሰው ስለዚህ ግድያ ለመመስከር ስለ ጠቡ ሁኔታ ማስታወስ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ባልና ሚስቱ ምን እየተባባሉ እንደተሰዳደቡ ወይም ገዳዩ ምን ዓይነት ጠብመንጃ እንደተጠቀመና ግድያውን በምን ሁኔታ እንደፈፀመው ያስታውሳል፡፡ በመጨረሻም ምስክሩ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የሰማውንና የተመለከተውን ሁኔታ ያስረዳል፡፡

የስሚ ስሚ ማስረጃ በቃል ማለትም በምስክር ለፍርድ ቤት ሊነገር ይችላል፡፡ በስሚ ስሚ ማስረጃ ምስክሩ የሚመሰክረው ራሱ በቀጥታ ስለሰማው፣ ስለዳሰሰው፣ ስለተመለከተው አሊያም ስለቀመሰው ነገር አይደለም፡፡ የስሚ ስሚ ምስክር የሚመሰክረው ፍርድ ቤት ያልቀረበ ሌላ ሰው ስለ ኩነቱ የተመለከተውን፣ የዳሰሰውን፣ የሰማውን አሊያም የቀመሰውን ነግሮት ወይም ሲናገር ሰምቶ ነው፡፡ ስለዚህ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቀጥተኛ ማስረጃ አይደለም፡፡ ብቁነቱም የሚመሠረተው ስለጉዳዩ ለፍርድ ቤት በሚመሰክረው ሰው ብቃት ብቻ ላይ ሳይሆን ስለ ኩነቱ በቀጥታ በተመለከተው፣ በሰማው፣ በቀመሰው፣ ባሸተተው አሊያም በዳሰሰውና በምስክርነት ፍርድ ቤት ባልቀረበው ሰው ብቃት ላይም ነው፡፡[20]

በግል ተበዳይ ላይ ድንጋይ በመወርወር የማቁሰል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በእንግሊዝ ፍርድ ቤት አንድ ተከሳሽ የተከሰሰበት ጉዳይ[21] ክሱ በሚሰማት ጊዜ፣ የግል ተበዳዩ ተከሳሽ ድንጋዩን ሲወረውር በዓይኑ እንዳየው ገልጾ ሆኖም ግን በድንጋይ እንደተመታ ወዲያውኑ አንዲት ሴት ወደተከሳሹ ቤት እያመለከተች የምትፈልገው ሰው እዚህ ቤት ገብቷል በማለት እንደነገረችው መስከሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ይህን ማስረጃ በመቀበል ተከሳሹ ጥፋተኛ ነው በማለት ወሰነ፡፡ ተከሳሽ ይግባኝ በማለቱ ሴትየዋ ተናገረች የተባለው ማስረጃ የስሚ ስሚ ስለሆነ በስሚ ስሚ ማስረጃ ደንብ መሠረት ቅቡልነት የለውም በማለት ይግባኝ ሰሚው

[17] Batuk Lal, (2001), *The Law of Evidence* (Fifteenth Edition), Central Law Agency, p. 248.

[18] *Ibid.*

[19] Walts, *supra* note 8, p. 11

[20] Lal, *supra* note 15, p. 250.

[21] R v. Gibson, (1887), in Law Reform Commision, (2010), (March 2010), *Consultation Paper- Hearsay in Civil and Criminal Cases*, accessed on 13/07/2012, p. 32.

ፍ/ቤት ተጠርጣሪውን በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በሌላ ውሳኔ[22] ደግሞ ተጠርጣሪው የራሱን ሱቅ በማቃጠል በተከሰሰበት ጉዳይ አንዲት ሴት ተከሳሹን በሚመስል የታክሲ ሾፌር ላይ በመጮህ ቤትህ እየተቃጠለ ትተህ ትሄዳለህ? ስትል እንደሰማት የዐቃቤ ሕግ ምስክር አስረዳ፡፡ የዳኝነት አካሉም ምስክርነቱ የስሚ ስሚ ስለሆነ ቅቡልነት የለውም ሲል ወሰነ፡፡

የአይርላንድ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ስለ ስሚ ስሚ ደንብ ተመሳሳይ አቋም ይዟል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በአንድ ጉዳይ[23] ከፍርድ ቤት ውጭ በምስክርነት ባልቀረቡ ሰዎች የተሰጡ መግለጫዎች የጉዳዩን ይዘት ለማረጋገጥ ከቀረቡ የስሚ ስሚ ስለሆኑ ቅቡልነት የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡

## 1.3. በጽሁፍና በድርጊት የተደረጉ የስሚ ስሚ መግለጫዎች

የስሚ ስሚ በቃል የተነገረውን ብቻ ሳይሆን በጽሁፍና በሰነድ የሰፈሩ መግለጫዎችንም ይጨምራል፡፡ ይህም እንደ ደብዳቤዎች፣ የሕክምና ዶሴዎች፣ የንግድ መዛግብት የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ በዚህም መሠረት በአንድ ጉዳይ[24] በሕክምና ቸልተኝነት ለደረሰ ጉዳት ካሳ ጥያቄ የሕክምና ዶሴዎች የቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ዶሴውን ያዘጋጁት ባለሙያዎች ቀርበው መስቀለኛ ጥያቄ ያልተጠየቁ በመሆኑ ቅቡልነት የላቸውም በማለት ማስረጃዎቹን ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ በይግባኝ ወደ ከፍተኛው ፍ/ቤት በቀረበበት ወቅት ተከራካሪዎቹ ማስረጃዎቹ ቅቡል እንዲሆኑ በመስማማታቸው ፍ/ቤቱ በፍትሐብሔር ጉዳይ የስሚ ስሚ ማስረጃን መቀበል አግባብ መሆኑን ገልጧል፡፡[25]

በአንድ የእንግሊዝ የወንጀል ጉዳይ[26] ተከሳሹ በሰው መግደል ወንጀል ተከስሶ ተወሰነበት፡፡ እርሱም በሚጥል በሽታ ተጠቂ እንደሆነ በመግለጽ የሐኪም ዶሴ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የሐኪም መዛግብቱ በርግጥ በሚጥል በሽታ ተጠቂ መሆኑን ቢያረጋግጡም፣ ያዘጋጁአቸው ሰዎች ፍ/ቤት ቀርበው መስቀለኛ ጥያቄ ያልቀረበባቸው የስሚ ስሚ ስለሆኑ ቅቡልነት የላቸውም በማለት ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶታል፡፡

ምልክቶች፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች፣ ሥዕሎች፣ ቻርቶችና ፎቶግራፎች በስሚ ስሚ ሥር ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የድርጊት መግለጫዎች የሰውየውን ሀሳብ የማያስረዱ ከሆነ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡ ሊድርማን እና ብርያንት እንደጻፉት ከመግለጫ ሰጭው ሀሳብ ውጭ የሆኑ የድርጊት መግለጫዎች በስሚ ስሚ ደንብ መሠረት ቅቡል ሊሆኑ አይገባም፡፡[27]

በመሆኑም የድርጊት መግለጫ በስሚ ስሚ ሥር የሚካተተው የተፈለገውን ሀሳብ (መግለጫ) የሚያስተላልፍ ሲሆን ነው፡፡ በበርካታ የ'ኮመን ሎው' ሀገሮች መግለጫ ሰጭው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ በሚመለከት የድርጊት መግለጫ በስሚ ስሚ ደንብ እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡[28] የእንግሊዝ ፍ/ቤቶች የስሚ ስሚ መርህን በ19ኛው ክፍለዘመን በማስፋፋት

---

[22] Law Reform Commision, *ibid*.

[23] In Cullen V. Clare, 1963, IE 368.

[24] In Hughes V. Staunton, High Court, (16 February 1990).

[25] In Common law, in the abcence of agreement, documentary records are, in general, inadmissible if introduced to prove their contents. See Law Reform Commission, *supra* note 19, p. 33.

[26] The People (Attorney General) V. O'Brien, 1969, in Law Reform Commission, *supra* note 19, p. 33.

[27] Law Reform Commission, *supra* note 19, p. 34.

[28] For instance Rule 801(a) of the US Federal Rules of Evidence provides that a 'statement' includes "nonverbal conduct of a person, if it is intended by the person as an assertion". See Law Reform Commission, *supra* note 19, p. 34.

በድርጊት የሚገለጽ የስሚ ስሚ እንዲያካትት አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በአንድ ጉዳይ[29] ደብዳቤ የመጻፍ ድርጊት የተከሳሹን አዕምሮ ጤንነት ለማሳየት ሲቀርብ ፍ/ቤቱ የስሚ ስሚ ነው በማለት ወስኗል፡፡

### 1.4. ሀሳብ (Intent) እና በአርምሞ የሚደረግ ማረጋገጫ

ስሚ ስሚ መስካሪው ከተሳሳተ ወይም ከዘባረቀ ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የእንግሊዝ የሕግ ማሻሻያ ኮሚሽን ገልጧል፡፡ ሆኖም ግን ሆን ተብሎ የሚፈበረክ ካልሆነ በቀር የስሚ ስሚ መስካሪው ስህተት በዚያው ስህተት በተደረገበት ጭብጥ ላይ ካልሆን በቀር የስሚ ስሚን ማስረጃ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ለማድረግ አያስችልም የሚል አቋም አለ፡፡ ከፍ/ቤት ውጭ የሚደረጉ መግለጫዎችን በሚመለከት ሆን ተብሎ ታሪክን የመፈብረክ ዕድል ካለ መግለጫው በግልጽም ሆነ በአርምሞ ቢደረግ በስሚ ስሚ ሥር የሚመደብና በማስረጃነት ቅቡልነት የሌለው ነው፡፡[30]

በአርምሞ የተደረገ መግለጫ የሚባለው የመግለጫውን ዕውነትነት ለማረጋገጥ ሳይሆን ለመግለጫው አንድ ዓይነት ትርጉም ለመስጠት የተደረገ ነው፡፡ በድርጊት የተደረገ መግለጫ የአንድን ኩነት እውነትነት ለማረጋገጥ የተደረገ ከሆነ፣ በስሚ ስሚ መርህ መሠረት ቅቡልነት የለውም፡፡

በእንግሊዝ የስሚስሚ ማስረጃ በፍትሐብሔር ጉዳይ ቅቡልነት አለው፡፡[31] በአይርላንድ ሕገመንግሥት ውስጥ የተካተተው መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት የስሚ ስሚ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ ለመፍቀድ የማያስችል መሆኑን በአንድ ወቅት የተቋቋመ የሕግ ኮሚሽን ገልጧል፡፡[32] ሌላው መጤን ያለበት ጉዳይ የእምነት ቃል በስሚ ስሚ ሥር የማይካተት መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የእምነት ቃል ከስሚ ስሚ ውጭ ነው፡፡[33]

## 2. የስሚ ስሚ ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ያለው ግንኙነት

አንድ ነገር የተፈፀመ ስለመሆኑ ነገሩን ራሱን በማቅረብ፣ በሰው ምስክር ማለትም ነገሩን ባዩት፣ በተመለከቱት ወ.ዘ.ተ ሰዎች ምስክርነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያስፈልግ አንድን ኩነት በቀጥታ የማረጋገጥ ችሎታ ያለው ማስረጃ ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል፡፡[34]

አንድን ኩነት ለማስረዳት ቀጥተኛ ማስረጃ በሌለ ጊዜ አካባቢያዊ ማስረጃ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት ቀጥተኛ ማስረጃ ላይኖር ይችላል፡፡ በአነፃሩ ግን ጠንካራ አካባቢዊ ማስረጃ ሊኖር ስለሚችል ይህን ማስረጃ መጠቀም ይገባል፡፡[35] የአካባቢ ማስረጃ በርካታ ነጥቦችን የሚያካትትና በእነዚህም ነጥቦች አማካኝነት ወደ አንድ መደምደሚያ እንድንደርስ የሚያስችለን ነው፡፡ በየራሳቸው የማሳመን ጥንካሬአቸው ደካማ የሆኑ የአካባቢ

---

[29] Wright V. Doed Tatham, (1838), in Law Reform Commission, *supra* note 19, p. 38.

[30] Law Reform Commission, *supra* note 19, p. 39.

[31] *Ibid,* p. 40

[32] *Ibid*, p. 169.

[33] It was explained by the Advisory Committee of the American Evidence Rules as "admissions by a party opponnent are excluded from the category of hearsay on the theory that their admissibility in evidence is the result of the adversary system rather than satisfaction of the conditions of the hearsay rule". Advisory Committee's note, p. 19.

[34] Richard May, (1995), *Criminal Evidence* (Third Ed), pp. 4-5.

[35] ሲ.ሰ.ማ.ፕ፣ (1994 ዓ.ም)፣ *የሥነ ምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም፣* ጥራዝ 2/ክፍል 2/ገጽ 268-269

ማስረጃዎች በአንድነት ሲመዘኑ የተሻለ የማሳመን ጥንካሬ ሊኖራቸው ይችላል።[36] ለምሳሌ፣ በወንጀል ጉዳይ የተጠርጣሪው የእግር ዱካ፣ ደሙ፣ ፀጉሩ፣ ልብሱ፣ እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች፣ አንድ ላይ በመሆን ተጠርጣሪው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ሊያረጋግጡ ይችላሉ። የአካባቢ ማስረጃ በአንድ ክስ ውስጥ ለሚነሱ ጥያቄዎች የግድ ሙሉ ምላሽ የሚሰጥ መሆን የለበትም። ያም ሆኖ ግን፣ ተጠርጣሪው የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጽሟል ወደሚል እርግጠኛ ድምዳሜ የሚያመራ መሆን አለበት።[37]

ቀጥተኛ ማስረጃ ጠንካራ ማስረጃ በመሆኑ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያስፈልግ በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ነው። ምክንያቱም የምስክሩ ዕውቀት ቀጥተኛ ነው። ነገር ግን የምስክሩ ማስረጃ በቂ ካልሆነ፣ ከቀረበው ማስረጃ በተጨማሪ ኩነቱን በቀጥታ ያልተገነዘበ የሌላ ሰው ማስረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ማስረጃው የስሚ ስሚ ማስረጃ እንደሚሆን የማስረጃ ሕግ ምሁራን[38] ጽፈዋል። ከነዚህ ምሁራን ትንታኔ እንደምንረዳው አካባቢያዊ ማስረጃ የስሚ ስሚ ማስረጃን ያካትታል።

## 2.1. የስሚ ስሚ ማስረጃ እና የአካባቢያዊ ማስረጃ

ከላይ እንደተመለከትነው አካባቢያዊ ማስረጃ የስሚ ስሚን ይጨምራል። ይሁን እንጂ አካባቢያዊ ማስረጃ ከስሚ ስሚ ማስረጃ ጋር ተመሳሳይ አይደለም። ‹ሀ› ‹ለ›ን ገድለሃል ተብሎ ክስ ቀርቦበታል እንበል። ‹ሀ› ‹ለ›ን ሲገድለው ‹መ› የተመለከተ ስለመሆኑ የምስክርት ማስረጃ ሰጠ። ይህ የ‹መ› የምስክርነት ማስረጃ ቀጥተኛ ማስረጃ ነው። በሌላ በኩል ‹ሠ› የሚባል ሰው ‹ሀ› ‹ለ›ን የገደለው ስለመሆኑ ‹መ› ነግሮኛል በማለት ቢመሰክር የ‹ሠ› ምስክርነት የስሚ ስሚ ማስረጃ ነው። ‹ሀ› የ‹ለ› አስከሬን ከተገኘበት ቤት ውስጥ ሲወጣ፣ በደም የተነከረ ስለት /ቢላዋ/ ይዞ የተመለከተው ስለመሆኑ ‹ሠ› ቢናገር ይህ ‹ሀ› ‹ለ›ን የገደለው ስለመሆኑ አካባቢያዊ ማስረጃ ነው። አካባቢያዊ ማስረጃ ከስሚ ስሚ ማስረጃ የተለየ ሲሆን ለፍርድ ቤት ሲቀርብ በቀጥተኛ ማስረጃ መደገፍ ያለበት ስለመሆኑ ባቱክ ላል የተባለ የሕግ ምሁር ጽፏል።[39]

## 2.2. የስሚ ስሚ ማስረጃና የባለሙያ ማስረጃ

'ልዩ አዋቂ'፣ የሚለው ቃል 'ኤክስፐርት' የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል እንደሚተረጉም ይታወቃል። ከዚህም ሌላ 'ኤክስፐርት' የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል።[40] "ኤክስፐርት" የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በአንድ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የኪነጥበብ ወይም ሌላ የሙያ መስክ ጠለቅ ያለ ምርምርን ያከናወነ ወይም ትምህርት የቀሰመን ሰው ያመለክታል።[41] የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ 'ባለሙያ' የሚለውን ቃል ለመጠቀም መርጧል።

ባለሙያ ምስክር (expert witness) የሚባለው ሙያዊ እውቀቱን፣ ጥበቡን፣ ሥልጠናውን ወይም ትምህርቱን በመጠቀም ስለቀረበው ማስረጃ ወይም በጭብጥ ስለተያዘው ኩነት ልዩ (ሙያዊ) አስተያየት ለመስጠት ብቃት ያለው ምስክር ነው።[42] ባለሙያ በአንድ ጉዳይ ላይ በትምህርት ወይም በሥራ ልምድ የዳበረ እውቀት ያለው ሆኖ የተለየ እውቀት በሚያስፈልገው

---

[36] ዝኒ ከማሁ

[37] ዝኒ ከማሁ፣ 169

[38] Lal, *supra* note 15, p. 253

[39] *Ibid.*

[40] የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 124/1/፣ 136/2/ን ይመልከቱ።

[41] Rogers, (1891), *Expert Testimony*, ($2^{nd}$ ed), p.2.

[42] Black, *supra* note 4, p.1697

ጉዳይ ላይ አስተያየት በመስጠት ስለ ኩነቱ የሚያጣራውን የፍትሕ አካል (ሰው) የሚረዳ ነው፡፡[43]

በእንግሊዝ ሀገር በስሚ ስሚ ደንብ መሠረት አንድ ባለሙያ በሌሎች ሰዎች ረዳትነትና ሀሳብ እንዲሁም ሳይንሳዊ ቁሳቁሶች ላይ በመመሥረት የሚሰጠው አስተያየት የስሚ ስሚ ስለሆነ በማስረጃነት ቅቡልነት የለውም፡፡ ሆኖም ግን የሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች ከተሟሉ የባለሙያ ማስረጃ በልዩ ሁኔታ (exception) ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ሁኔታዎቹም፣[44]

ሀ) ባለሙያው የሚሰጠው ሙያዊ አስተያየት ምንም እንኳ በራሱ የተገኘ ባይሆንም የሙያውን ዕውቀት የሚመለከት ከሆነ ቅቡልነት አለው፡፡ በመሆኑም አንድ ባለሙያ በሙያው መሠረት አንድ መድሀኒት ፔኒሲሊን ስለመሆኑ እንዲመሰክር በእንገሊዝ ሀገር ተፈቅዶለታል፡፡

ለ) የባለሙያው ምስክር በሙያው በስፋት ጥቅም ላይ የዋለና ተዓማኒነት ያለው ቴክኒካዊ መግለጫን በመጠቀም መሠረታዊ በሆኑ ኩነቶች ላይ በመመሥረት አስተያየቱን መስጠት ይችላል፡፡

መ) በወንጀል ጉዳይ አዘጋጁ በሌለበት አንድን ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ ለማብራራት ይችላል፡፡[45]

ከላይ እንደተመለከትነው አንድ ባለሙያ አስተያየቱን የሚሰጠው ሌሎች ሰዎች ስለኩነቱ በሰጡት መረጃ (information) ላይ ተመሥርቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ፓቶሎጂስት ስለሰውነት ጡንቻዎች እና የሆድ ውስጥ ዕቃዎች የሚሰጠው ሙያዊ አስተያየት ሌሎች ሰዎች በሰጡት መረጃ ላይ ሊመሠረት ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት የባለሙያ ምስክሩ ስለአንድ ፍሬ ነገር ለፍርድ ቤት የሚሰጠው የባለሙያ ምስክርነት ስለጉዳዩ የመጀመሪያ (ቀጥተኛ) እውቀት በሌለው ኩነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ የምስክርነት ማስረጃው የስሚ ስሚ ማስረጃ ሥር ይመደባል፡፡[46]

በጥቅሉ በ"ኮመን ሎው" የሕግ ሥርዓት መሠረት ባለሙያ ምስክርነት ተቀባይነት እንዲያገኝ አስተያየት የሚሰጥባቸው ማስረጃዎች ቅቡልነት ያላቸው እና ከሌሎች ሰዎች የመነጩ መሆናቸው በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥንካሬያቸውንና የድምዳሜቸውን ብቃት ለመመዘን እንዲቻል በመስቀለኛ ጥያቄ የሚጣሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡[47]

## 3. ምስክርን የመጋፈጥ መብት[48]

### 3.1. ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ትርጓሜና ወሰን

ማስረጃን የመጋፈጥ መብት በግልጽ ችሎት የመዳኘት፣ ምስክርን ፊት ለፊት የመጋፈጥ፣ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ፣ የአቤቱታ አቅራቢ (ከሳሽ)ን ማንነት የማወቅ መብቶችን አጠቃሎ ይይዛል፡፡[49] ተከሳሽ የቀረበበትን ማስረጃ ለመጋፈጥ ያለው መብት የሚዛናዊ የክስ መሰማት አካል እንደሆነ በስፋት ስምምነት አለ፡፡ ይሁን እንጂ መጋፈጥ ማለት ምን ማለት እንደሆነ

---

[43] *Ibid,* p. 600.

[44] Mrs. Justice Arden (Chairman), (1996), *The Law Commission Evidence in Criminal Proceedings: Hearsay and Related Topics*, accessed on 13/07/2012, p. 135-6.

[45] For detailed considerations see R. Pattenden, "Expert Opinion Evidence Based on Hearsay" (1982), *Crim.L.R,* p. 85.

[46] ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ *ከላይ* በቁጥር 35 የተጠቀሰ፣ ገጽ 282

[47] ዝኒ ከማሁ

[48] ይህ መብት በእንግሊዝኛ "The Right to Confrontation" ይባላል፡፡

[49] Ian Dennis (2010), "The Right to Confron Witnesses: Meanings, Myths and Human Rights", *Crim. L.R.* (Thomson Reuters (Legal) Limited), pp.255-56.

ስምምነት የለም። በአሜሪካ ለዚህ ጽንሰ ሀሳብ ከእንግሊዝና ከአውሮፓ የሰብአዊ መብት ስምምነት ውስጥ ከተደነገገው የተለየ ትርጓሜ ተሰጥቶታል። በጥቅሉ ማስረጃን የመጋፈጥ መብት መኖር እንዳለበት የታመነ ቢኖርም ድንበሩ ምን ድረስ እንደሆነ ግን ስምምነት የለም። ስለሆነም አንድ ይዘትና ትርጉም ያለው የመጋፈጥ መብት ማግኘት አስቸጋሪ ነው። በተጨማሪም ይህ መብት በተለያዩ ገደቦችና ልዩ ድንጋጌዎች የተከበበ በመሆኑ ፍፁማዊ መብት ካለመሆኑም ባሻገር አድማሱ እየጠበበ መጥቷል። የማስረጃ ሕጎች በርካታ የስሚ ስሚ ልዩ ድንጋጌዎችን እያሰፉ ከመሆናቸው በተጨማሪ የምስክሮችን ማንነት ያለመግለጽ መብት በሕግ እየተደነገገ ነው።[50]

ማስረጃን የመጋፈጥ መብት አስፈላጊነትን በተመለከተም የተለያዩ ኣቋሞችን እናገኛለን። በዚህ ረገድ የመጋፈጥ መብት እንደንፁህ ከመቆጠር መብት ይለያል። ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በማቅረብ ክሱን ሲያሰማ ተከሳሹ የቀረበበትን ማስረጃ መመርመር እንዳለበት ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ያመለክታል። ተከሳሹ ምስክሮችን መጋፈጥ እንደሚፈልግ ሁሉ ምስክሮች ደግሞ ፍላጎቶቻቸው እንዲከበሩላቸው ይፈልጋሉ። በአንድ በኩል የፖለቲካ ተፅእኖን ለመከላከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተከሳሹን መብት ለማስከበር ሕጉ ቅድሚያ መስጠት ያለበትን ጥቅም በመለየት ለችግሩ መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ግን እጅግ ከባድ ነው።[51]

የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ ስለ ስሚ ስሚና ማስረጃን ስለመጋፈጥ መብት ግንኙነት ሲያትት ሁለቱም የሚጠብቋቸው እሴቶች ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ሁለቱም ሙሉ በሙሉ አንድ ናቸው ማለት አይቻልም፤ በስሚ ስሚ ልዩ ድንጋጌዎች መሠረት ማስረጃዎች እንዲቀርቡ መፍቀድ ማስረጃ የመጋፈጥ መብትን ይቃረናል ብሏል።[52]

## 3.1.1. በግልጽ ችሎት የመዳኘትና ፊት ለፊት የመጋፈጥ መብት

በግልጽ ችሎት በመዳኘት መብት መሠረት ማስረጃ የሚሰማው ተከሳሹ ባለበት በግልጽ ችሎት መሆን አለበት። የዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ሚዛናዊ በሆነ ግልጽ ችሎት የመዳኘት መብትን ደንግገው እናገኛለን።[53] ቤንታም እንደሚለው፣ በግልጽ ችሎት የመዳኘት መብት አስፈላጊነት ሸፍጠኝነትን በማስቀረት የምስክርነት ቃል ትክክለኛ እንዲሆን ይረዳል። ይህ መርህ ምስክሮች ሀቀኛና እምነት የሚጣልባቸው መሆናቸውን ለማጣራት የሚረዳና ተከሳሹ ምስክሮችን ለመመርመር ያለውን መብት የሚያረጋግጥ ከመሆኑም ባሻገር ለውሳኔው ትክክለኛነት አዎንታዊ አስተዋጽዖ ያደርጋል። ፍሬይድማን እንደገለፀው በግልጽ ችሎት የመዳኘት መብት መንግሥት ሕግን በመጣስ ከሕግ ውጭ ማስረጃን እንዳይሰበስብ ይከለክለዋል። ይሁን እንጂ የአውሮፓ የሰብአዊ መብት ኮንቬንሽን በግልጽ ችሎት በመዳኘት መብት ላይ ገደብ በማድረግ፣ የተከራካሪ ወገኖችን ምስጢር ለመጠበቅ ወይም ጉዳዩን በግልጽ ችሎት ማየቱ ፍትሕን የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ በዝግ ችሎት እንዲታይ ይፈቅዳል። ያም ሆነ ይህ የስሚ ስሚ ምስክርነት በሚቀርብበት ጊዜ ዋናው ተናጋሪ ለጥያቄ ስለማይቀርብ በግልጽ ችሎት የመዳኘት መብትን ይነካል።[54]

---

[50] *Ibid*, p. 261

[51] California V. Green, 399 U.S. 149, 155-56 in *Hearsay*, accessed on 13/07/2012, p. 8.2.

[52] See Dennis, *supra* note 49, pp. 261-73.

[53] See European Convention on Human Right, Art. 6(1); and International Covenant on Civil and Political Rights, Art. 14.

[54] Dennis, *supra* note 49, p. 262.

ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ፊት ለፊት የመጋፈጥ መብትን (the right to face-to-face confrontation) ስለሚጨምር ተከሳሹ የከሰሱትን ሰዎች ፊት ለፊት የማየት መብት አለው፡፡ ይህ መብት በአሜሪካ በ16ኛው ክፍለዘመን የመጋፈጥ መብት ሥር የተካተተ ሲሆን በእንግሊዝ ሕግና በአውሮፓ የሰብአዊ መብት ኮንቬንሽን ግን አልተካተተም፡፡ በፊት ለፊት የመጋፈጥ መብት መሠረት የግል ተበዳዩ ወይም አቤቱታ አቅራቢው ከመጋረጃ በስተጀርባ ሳይሆን በተከሳሹ ፊት ክሱን ማቅረብ አለበት፡፡ በተጨማሪም ምስክሮች መሃላ ፈጽመው በችሎት ፊት እየታዩ መመስከር አለባቸው፡፡ በመሆኑም ክስ የሚያቀርብ ሰው ከሚከሰው ሰው ፊት ቀርቦ የማሰማት ግዴታ አለበት፡፡ ሸርማን ክላርክ እንደጻፈው ሰዎች ፊት ቀርቦ እንጂ ጓዳ ለጓዳ መክሰስ አግባብነት የለውም፤ ሆኖም ግን ተከሳሹን ሲመለከቱ አግባብነት የሌላቸው ባሕሪዎች የሚንጸባረቁ ከሆነ ፊት ለፊት መቅረብ አያስፈልግም፤ የስሚ ስሚ ምስክሮችን ፊት ለፊት አግኝቶ መጠየቅ ስለማይቻል የስሚ ስሚ ማስረጃ ከዚህ መርህ ያፈነግጣል፡፡[55]

## 3.1.2. መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅና የከሳሽን (የአቤቱታ አቅራቢን) ማንነት የማወቅ መብት

ማስረጃን የመጋፈጥ መብት መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ የምስክሮችን ቃል ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ የመጣል መብትን ያካትታል፡፡ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት ተከሳሹ እውነቱን ለማሳየት ስለሚረዳው መሠረታዊ መብት ነው፡፡[56] መስቀለኛ ጥያቄ የማስረጃ ተዓማኒነትን ለመፈተሽ የሚያገለግል ነው፣ የኩነት ዳኞች (juries) ለማስረጃው የሚገባውን ክብደት በመስጠት ጉዳዩን ተረድተው ውሳኔ ለመወሰን ያስችላቸዋል፡፡ ይህ መብት ምስክር በመስማት ሂደት ተከሳሹ ተሳትፎ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡[57]

መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት በርካታ ገደቦች ያሉበት ሲሆን የወሲብን ጥቃት በሚመለከት አቤቱታ ሲቀርብ እንዲሁም የህጻናት ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡ በእንግሊዝ ሀገር አንዳንዴ የምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ምስክርነቱን ዋጋ የሚያሳንሰው ከሆነ ፍ/ቤቱ መስቀለኛ ጥያቄ እንዳይጠየቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ግን ጠበቃው ተከሳሹን በመወከል መስቀለኛ ጥያቄ እንዳይጠይቅ ስለማይከለክለው መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት ተቋማዊ እንጂ የግለሰብ መብት አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ሊያመራ ይችላል፡፡ አንዳንድ ጥያቄዎችንና ማስረጃዎችን በተመለከተ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት ሊገደብ ይችላል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች የሚሆኑት በመደፈር ጉዳይ ተበዳይ የሆኑ ሰዎች የወሲብ ታሪክን በሚመለከት ወይም የተበዳዮችንና የምስክሮችን የኋላ ታሪክ በሚመለከት መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ የማይቻል መሆኑ ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ የሚሰነዘሩት ጥያቄዎች ተገቢ ካልሆኑ ወይም ጨቋኝ ከሆኑ በመስቀለኛ ጥያቄነት እንዲቀርቡ አይፈቀድም፡፡[58]

የከሳሽን (የአቤቱታ አቅራቢን) ማንነት የማወቅ መብት የምስክሮችን ማንነት ካለመግለጽ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ አከራካሪ ነው፡፡ በመሠረቱ የምስክሮችን ማንነት ሳያውቁ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን ገቢራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡ ቢሆንም የምስክርን ማንነት ማወቅ የመስቀለኛ ጥያቄዎችን አድማስ ያሰፋዋል፡፡ ተከሳሹ የምስክሩን ማንነት ካላወቀ፣ ስለኋላ ታሪኩና ስለዝናው ስለማያውቅ መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ ይቸገራል፡፡ በስሚ ስሚ ጉዳይ

---

[55] *Ibid*, p. 264.

[56] Wigmore wrote that cross-examination is "beyond any doubt the greatest legal engine ever invented for discovery of truth," *Ibid,* p. 266.

[57] *Ibid*, p. 266.

[58] *Ibid*, p. 267.

የምስከሩ ማንነት ስለማይገለፅ መንግሥት ይህን ያለአግባብ ሊጠቀምበት የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል የሚል ስጋት አለ፡፡[59]

በጥቅሉ፣ ከላይ እንደተመለከትነው በአንድ በኩል ተከሳሽ ሊጠበቅለት የሚገባውን ማስረጃ የመጋፈጥ መብት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ መብቶችንና ጥቅሞችን ለማስከበር የሚኖረውን ፍላጎት በመመዘን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን መለየትና መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡[60]

## 3.2. ማስረጃን የመጋፈጥ መብት በ'ኮመን ሎው' ና በ'ሲቪል ሎው'

በ'ኮመን ሎው' የመጋፈጥ መብት የተከሰሰ ሰው የቀረቡበትን ምስክሮች ፊት ለፊት ቆመው የመመርመር መብት ስለሆነ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅን ይጨምራል፡፡ መሠረታዊ ጠቀሜታውም አቤቱታ አቅራቢ በተከሳሹ ፊት እንዲቆም ማድረግ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የምስክር ማስረጃውን ተዓማኒነት ለመመዘን ዕድል ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የመጋፈጥ መብት ከሳሹና ምስክሮች ምን እንዳሉ መስማት ብቻ ሳይሆን በፊቱ ቆመው የሚናገሩትን ማዳመጥ ስለሆነ የመጋፈጥ ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ ተከሳሹ  አቤቱታ አቅራቢዎች በፊቱ ቆመው በእሱ ላይ የሚናገሩትን ማዳመጥና የሰውነት ሁኔታቸውን ማየቱ ተገቢ ስለሆነ በተከሳሹ ፊት መመስከር አለባቸው፡፡ አንድ የአሜሪካ ፍ/ቤት እንዳተተው ይህን አለማድረግ የፍትሕ ውድቀት ነው፡፡[61] 'ኮመን ሎው' በተለይ በስሚ ስሚ መርህ ልዩ ድንጋጌዎች ሥር ማስረጃን የመጋፈጥ መብትን ገደቦች የተቀበለ ሲሆን ተናጋሪው በማይገኝበት ጊዜ ወይም ማስረጃው አስተማማኝ በሆነ ጊዜ የሚፎካከሩ ጥቅሞችን ማለትም ማስረጃን ለመጋፈጥ ተከሳሽ ያለውን መብት እና የፍትሕን ጉዳይ አጣጥመው የያዙ ናቸው፡፡[62]

በ'ሲቪል ሎው' ማስረጃን የመጋፈጥ መርህ ቢያንስ በጥንታዊ ሮም እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት የዘመናዊ የወንጀል አስተዳደር አንዱ ምሰሶና የፍትሐዊነት መመዘኛ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በ'ሲቪል ሎው' ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ከ20ኛው  ክፍለዘመን በፊት በቅጡ የማይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በጥያቄ የመመርመር ሥርዓት ገቢራዊ ተደርጓል፡፡ ማህበራዊ ሥርዓትን ለመጠበቅና የሕዝብ ተቃውሞ እንዳይነሳ ለማድረግ ማስረጃዎች በምስጢር ይያዙ የነበረ ከመሆኑም ባሻገር የምስክሮች ማንነት እንዳይታወቅ ይደረግ ነበር፡፡ ይህም በወንጀል ጉዳይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ለአታላይነት፣ ለሀሰተኛነትና ለወገናዊነት እንዲጋለጡ በር የከፈተ አሠራር ነበር፡፡ ተጠርጣሪዎች ማስረጃዎችን ለመፈተሽ ዕድል አልነበራቸውም፡፡[63]

በዘመናዊው 'ሲቪል ሎው' ግን ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ እኩል ጉልበት ይኑራቸው በሚል አስተሳሰብ ማናቸውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው ስለጉዳዩ እንዲነገረው፣ ማስረጃንም እንዲመረምር የሚያስችል መርህ[64] ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መብት ተከሳሹ የቀረቡበትን ማስረጃዎችና ክርክሮች በሙሉ እንዲያውቃቸው ለነርሱም ምላሽ እንዲሰጥባቸው ዕድል ይሰጠዋል እንጂ በቀጥታ ምስክሮችን የመመርመር መብትን አይጨምርም፡፡ በ'ሲቪል ሎው'

---

[59] *Ibid*.

[60] *Ibid*, p. 273.

[61] Kweku Vanderpuye (2010), "Traditions in Conflict: The Internationalazation of Confrontation", *Cornell Int'L L.J.*, Vol. 43 p. 524. ምስክሮች ፊት ለፊት ቆመው መመስከራቸው መዋሸት አለመዋሸታቸውን ከገጻቸው ለማንበብ ያስችላል፡፡

[62] *Ibid*.

[63] *Ibid*, p.521.

[64] It is the principle of the *Procedure contradictoire*- See Diane Marie Amann, Harmonic Convergence? Constitutional Criminal Procedure in an International context, (2000),75 *Ind. L.J.* 809, 835.

የማስረጃ ማግለልን የሚመለከቱ የማስረጃ ደንቦች እጅግ ጥቂት በመሆናቸው ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ብዙም ትኩረት የተሰጠው አይደለም፡፡[65]

## 4. የስሚ ስሚ ማስረጃ በ'ኮመን ሎው

### 4.1. የስሚ ስሚ ማስረጃ ክፍተቶች

በ'ኮመን ሎው' የሕግ ሥርዓት የስሚ ስሚ ማስረጃን በሚመለከት ደንብ (rule) አለ፡፡ ይህ የስሚ ስሚ ደንብ ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጡ መግለጫዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን ስለ አንድ ኩነት የተሰጠው መግለጫ በቃል፣ በሰነድ፣ በድርጊት (conduct)፣ በቀጥታ አሊያም በአንድምታ (implied) ሊሆን ይችላል፡፡[66] በ'ኮመን ሎው' የስሚ ስሚ ደንብ መሠረት አንድ የምስክርነት ማስረጃ በፍትሕ መንበር መቅረብ ያለበት (በሕግ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር) መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ ለማረጋገጥ ዕድሉ ካለ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ደንብ መሠረት የስሚ ስሚ ምስክርነት በመርህ ደረጃ ቅቡልነት የሌለው ቢሆንም እንኳ በርካታ ቁጥር ያላቸው ልዩ ድንጋጌዎች ስላሉ የስሚ ስሚ በልዩ ሁኔታ (exception) ቅቡልነት ይኖረዋል፡፡[67]

የስሚ ስሚ ማስረጃ ዋጋ የሚመሠረተው ፍርድ ቤት ችሎት በቀረቡ ሰዎች ሳይሆን ፍርድ ቤት ባልቀረቡ በሌሎች ሰዎች እውነተኛነት ላይ ነው፡፡ በመርህ ደረጃ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት የሌለው ማስረጃ ነው፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነትን ያጣው በሚከተሉት ሕጸጾች[68] የተነሳ የማይታመንና እውነተኛነቱ አጠራጣሪ በመሆኑ እና በወንጀል ጉዳይም የተከሳሽን መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት የሚገድብ በመሆኑ ነው፡፡ ይኸውም፣

1. **ፍ/ቤት ያለመቅረብ-** ዋና ተናጋሪው ፍ/ቤት በኩነት ዳኞች (Jury) ፊት ቀርቦ ስለማይመሰክር ያለውን የሰውነት አቋም ለመገምገም አይቻልም፡፡ ምስክሩ ቃሉን ሲሰጥ በአካል መመልከቱ ምን ያህል እውነትና ትክክለኛ ቃል እየተናገረ ስለመሆኑ ሰውነቱን (ፊቱን)ና ድርጊቱን በማየት የኩነት ዳኞች እንዲረዱት ይረዳቸዋል፡፡
2. **በቃለ መሃላ ያልተሰጡ መሆናቸው-** በስሚ ስሚ ጊዜ የመጀመሪያው ተናጋሪ ከፍርድ ቤት ውጭ መግለጫውን የሚሰጠው እውነቱን ለመናገር የማረጋገጫ ቃል ሳይሰጥ ወይም የመሃላ ቃል ሳይፈጽም ነው፡፡ ምስክሮች የምስክርነት ቃል መስጠት ያለባቸው ቃለ-መሃላ ፈጽመው ሲሆን ቃለ መሀላ ምስክሩ በእውነት የመመስከር ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና የሀሰት ምስክርነት መስጠት ያለውን አደጋ ማስገንዘብ ነው፡፡ የስሚ ስሚ ዋናው ተናጋሪ ቃለመሃላ ሳይፈጽም ስለሚናገር ይህ ሁኔታ አይኖርም፡፡[69]

---

[65] Vanderpuye, *supra* note 61, Pp. 522-23.

[66] See generally Seabooke Stephene and John Spack; (1999), *Criminal Evidence & Procedure: The Essential Framework,* (Blackstone, London).

[67] Blacks, *supra* note 4, p. 726.

[68] Hydoc Roger and Sonsteng John, (1995), *Evidence, Objections and Exhibits* (West Publishing Co.), p. 77; David H. Taylor, *Hearsay and the Right of Confrontation in American Trials by Jury*, accessed on 12/08/2012, Pp. 13-5.

[69] የዚህች ጽሑፍ አዘጋጅ ባንድ ወቅት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጠበቃነት በቆመበት ጊዜ አንድ የሙስና ወንጀል ሲሰማ ምስክሮች ቃለ መሃላ እንዲፈጽሙ ሲጠየቁ ከምስክሮች አንዱ መሃላ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱም ምክንያቱን ሲጠይቀው የምምል ከሆነ ዐቃቤ ህግ የነገረኝን ሳይሆን እውነቱን ነው የምመሠክረው አለ፤ በዚህም የተነሳ ዐቃቤ ሕጉ ምስክርነቱን አልፈልግም በማለት ትቶታል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ እንደተቀመጠው ምስክር መማል ያለበት "በዚህ ፍ/ቤት ፊት የምሰጠው ቃል እውነት፤ በሙሉ እውነት እውነት እንጂ ሌላ ምንም እንደማይሆን እምላለሁ(ወይም አረጋግጣለሁ)" በማለት ነው፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ገጽ 77 ላይ ይመልከቱ፡፡

3. ***መስቀለኛ ጥያቄ-*** *የመጀመሪያው ተናጋሪ ፍርድ ቤት ስለማይቀርብ መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ ዕድል የለም። መስቀለኛ ጥያቄ እውነትን አንጥሮ ለማሳየት ዋና መሳሪያ ሆኖ ሳለ፣ በስሚ ስሚ ወቅት መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ ዕድል አለመኖሩ የስሚ ስሚን ቅቡልነት እንዳይኖረው ዋናው ምክንያት ነው። መስቀለኛ ጥያቄ ምስክሩ አድሎአዊ ስለመሆኑ፣ የመመልከት፣ የማጤን፣ የማስታወስና የግልጽነት ችግር ያለበት ስለመሆኑ ለማሳየት ያስችላል። ከጉዳዩ የሚጠብቀው ጥቅም ስለመኖሩ፣ ከተከራካሪዎች ጋር ጠብና ዝምድና እንዳለው ለመጠየቅ ያስችላል። በተጨማሪም ስለሚመሰክረው ጉዳይ የግል ዕውቀት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ እና ስለኩነቱ ለማወቅ በቂ ዕድል የነበረው ስለመሆን አለመሆኑ በመስቀለኛ ጥያቄ ይጠየቃል።*
4. ***የምስክር መልካም ስም-*** *በመስቀለኛ ጥያቄ ስለምስክርነቱ ትክክለኛነት ከመፈተሽ በተጨማሪ ምስክሩ እውነቱን ላለመናገር ስላለው ጠባይ ለመፈተን የማስረጃ ደንቦች ይፈቅዳሉ። ምስክሩ ለታማኝነት ተቃራኒ በሆነ ወንጀል ወይም በመሰል ወንጀል ቀደም ሲል የተፈረደበት ስለመሆኑም ማሳየት ይቻላል። በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ምንም እንኳ ከጉዳዩ ጋር የማይገናኝ ቢሆንም ምስክሩ እውነት ተናጋሪ ስላለመሆኑ መጠየቅ ይቻላል። ከዚህም ባሻገር ታማኝ አለመሆኑን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል። ይህ ግን የምስክሩን ጠባይ የሚመለከቱ ኩነቶችን ብቻ ስለመሆኑ ሊጤን ይገባል።*[70]

*በአጭሩ*[71] *ለምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ መቅረቡ እንዲሁም የምስክሩ ጠባይ፣ ሁኔታ፣ እውነት የመናገርና ያለመናገር ባሕርይ፣ ወዘተ .. ባንድነት ሆነው ለምስክርነት ትክክለኛነትና ምልዑነት ዋስትና ተደርገው ይወሰዳሉ። በአንፃሩ ከፍርድ ቤት ውጭ የተገኙ መግለጫዎችን ወይም ድርጊቶችን ለመፈተሽ ይህ ዕድል ስለማይኖር የስሚ ሰሚ ማስረጃ በ'ኮመን ሎው' የሕግ ሥርዓት በመርህ ደረጃ ተቀባይነት የለውም።*

*ከፍርድ ቤት ውጭ የሚሰጡ መግለጫዎች የሚከተሉት አራት አደጋዎች የተጋረጡበት ነው። እነርሱም፣ መግለጫውን በአግባቡ ያለመረዳት፣ የማስታወስ ችሎታ የመሳሳት፣ በአግባቡ የመግለጽ ብቃት አለመኖር፣ እና መግለጫውን የማፋለስ አደጋዎች ናቸው። ሆኖም ግን የስሚ ስሚ ማስረጃን ሙሉ በሙሉ ዋጋ ማሳጣት ማስረጃ የማቅረብ ነፃነትን ይገድባል፣ ይቃረንማል።*[72]

## 4.2. የስሚ ስሚ ማስረጃና ማስረጃን የመጋፈጥ መብት አጀማመርና ዕድገት በ'ኮመን ሎው'

*የስሚ ስሚ የሚለው ቃል የሕግ ባለሙያ ባልሆነው የማህበረሰብ አባል ዘንድ መረጃው ሁለተኛ የሆነና ምናልባትም ዕምነት የሌለው ሀሳብን የሚያንጸባርቅ ነበር። በሕግ ሙያ ዘንድ ደግሞ የስሚ ስሚ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ የ'ኮመን ሎው' ፍ/ቤቶች እንደፈጠሩት የምርምር ጽሁፎች ያስረዳሉ። እ.ኤ.አ በ1813 ማርሻል የተባሉ ዳኛ እንደጻፉት የስሚ ስሚ ማስረጃ በተፈጥሮው ቅቡልነት የለውም። ምክንያቱም የኩነትን መኖር የማስረዳትና አዕምሮን የማሳመን ብቃት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር ለሸፍጥና ለመጥፎ ነገር የተጋለጠ ነው።*[73]

*አንድ ተከሳሽ የቀረበበትን ማስረጃ ለመመርመር ያለው መብት በአሜሪካ ሕገመንግሥት ሲደነገግ መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ ምስክሮችን የመመርመር መብት አብሮ ብቅ አለ። ይህም*

---

[70] *በኢትዮጵያ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/* 149(3) *እና* (4) *እንደተደነገገው በዋናው ጉዳይ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ቅጣት ለማክበድ ወይም ለማቅለል የተከሳሹን ጠባይ የሚመለከቱ ማስረጃዎችን በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል የተደነገገው ምስክሮችን አይመለከትም።*

[71] Taylor, *supra* note 68, p. 15.

[72] Chang, *supra* note 9, p. 18.

[73] *Ibid*, p. 16.

ምስክሮችን የመመርመር ሕገመንግሥታዊ መብት ዕምብርት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እ.ኤ.አ በ1807 ማርሻል የተባሉት ዳኛ በአንድ ጉዳይ[74] እንደገለፁት ማስረጃን የመመርመር መብት የስሚ ስሚን ቅቡልነት ይገድባል፡፡ ፕሮፌሰር ራንዶልፍ እንደጻፉት፣ የስሚ ስሚ ደንብ ምስክርን የመመርመር መብት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ደንቡም መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን ያረጋግጣል፡፡ በ6ኛው የአሜሪካ ሕገመንግሥት ማሻሻያ መሠረት ማስረጃን መመርመር ሕገመንግሥታዊ መብት ነው፡፡[75]

እ.ኤ.አ. በ1968 የአሜሪካ ፍ/ቤት በአንድ ጉዳይ፣ ማስረጃን የመመርመር መብት የክርክር መስማት መብት አካል መሆን አለበት፤ ይህም ምስክሩ የማይገኝ ካልሆነ በስተቀር መስቀለኛ ጥያቄን የመጠየቅ መብትን የሚያጎናጽፍ መሆን አለበት፤ በቅድመ ምርመራ ፍ/ቤት ብቻመስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን መወሰን ማስረጃ የመመርመር መብትን የሚጥስ ነው ብለዋል፡፡ ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ከስሚ ስሚ የሰፋ ሲሆን፣ እውነትን ከማፈላለግ በተጨማሪ ፍትሐዊነትንና ተጠርጣሪው የቀረበበትን ማስረጃ (የፈለገውን ያህል ተዓማኒ ቢመስልም) የመፈተሽ ዕድልን ያካትታል፡፡[76]

ስለሆነም ምስክሩ የሚገኝ ከሆነ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ፍ/ቤት ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን መስጠትና በተጠርጣሪው መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ አለበት፡፡ በመሆኑም ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጠ ምስክርነት ቅቡልነትን እንዲያገኝ ምስክሩ የማይገኝ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ ሆኖም የአሜሪካ ፍ/ቤት በሌሎች ጉዳዮች ይህን ጥብቅ መመዘኛ ውድቅ አድርጎታል፡፡[77] በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሁለት መመዘኛዎችን አስቀምጧል፡፡ የመጀመሪያው መመዘኛ ተናጋሪው ፍ/ቤት ለመስቀለኛ ጥያቄ ለመቅረብ የሌለ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤ ማስረጃውም ተዓማኒ እስከሆነ ድረስ ቅቡልነት አለው፡፡ የማስረጃው ተዓማኒነት አንድን ማስረጃ ከስሚ ስሚ ደንብ በተለየ መልኩ ቅቡል ለማድረግ እንደመመዘኛ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ መግለጫው ተዓማኒ ካልሆነ ቅቡልነት ሊኖረው አይገባም፡፡ በመሆኑም ማስረጃን በመጋፈጥ ወይም በመመርመር መብት መሠረት ሊገኝ የማይችል(የሌለ ሰው) መግለጫ ተአማኒ እስከሆነ ድረስ ከፍ/ቤት ውጭ በመሰጠቱ ብቻ ውድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡ ይሁን እንጂ ከፍ/ቤት ውሳኔዎች እንደምንገነዘበው የሁለቱ መመዘኛዎች ገቢራዊነት አጠያያቂ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ በግንባር ሊቀርብ ከማይችል ሰው የተገኘን ማስረጃ በልዩ ሁኔታ (exception) የስሚ ስሚ እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት የሚችል ቢሆንም፣ ተዓማኒነቱ ግን ሁሌ መሟላት አለበት፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ሲሆን በሌላ ፍ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ቅቡልነት አለው፤ ዐቃቤ ሕግም ምስክሩ የማይገኝ መሆኑን ማረጋገጥ አይጠበቅበትም በማለት ወስኗል፡፡ በአሜሪካን ሕገመንግስት 6ኛ ማሻሻያ ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ማለት ፊት ለፊት በአካል መመርመር ብቻ ላይሆን ይችላል የሚል ትርጉም ፍ/ቤቱ ሰጥቶታል፡፡[78]

በመቀጠልም በ2004 (እ.ኤ.አ) የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሌላ አዲስ መመዘኛ አስቀምጧል፤ ይህም ማስረጃው ተዓማኒ መሆን ብቻ ሳይሆን በመስቀለኛ ጥያቄ መረጋገጥ አለበት የሚል ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የስሚ ስሚ በቃል፣ በሠነድ አሊያም በድርጊት ሊገለጽ ይችላል፡፡ መግለጫውን በመስቀለኛ ጥያቄ የማረጋገጥ መመዘኛ የሚሠራው ማስረጃው የሚነገረው

---

[74] *States v. Burr*, in Chang, *ibid*, p. 10.

[75] *Ibid*, p. 10-1.

[76] *Ibid*, p.12.

[77] In Dutton V. Evan, under Snyder V. massachussetts the Cout stated that the mission of the confrontation Cluase is to advance a practical concern for the accuracy of the truth- determining process in criminal trials by assuring that 'the trier of fact has a satisfactory basis for evaluating the truth of the prior statement', See Chang, *ibid*, p. 13.

[78] Chang, *ibid*, p. 14-5.

በምስክር ከሆነ ነው፡፡ ስለሆነም 6ኛው የሕገመንግሥቱ ማሻሻያ በምስክር ለሚነገር ማስረጃ ይሠራል፡፡[79]

ከላይ ከተደረገው ማብራሪያ እንደምንገነዘበው የስሚ ስሚ ማስረጃ ደንብና መመዘኛ በየጊዜው እየተለዋወጠ በመምጣቱ የተነሳ መመዘኛው ይሄ ነው ብሎ ማስቀመጥ ያስቸግራል፡፡ ይህም የጽንሰ ሃሳቡን ውስብስብነትና ለመረዳትም አስቸጋሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሆኖም ግን ማስረጃውን ቅቡል ለማድረግ የስሚ ስሚ ማስረጃ ተዓማኒነት እና መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ ዕድል መኖር አስፈላጊ መመዘኛዎች ናቸው፡፡

## 4.3. በ'ኮመን ሎው' የስሚ ስሚ ማስረጃ በተለየ ሁኔታ ቅቡል ስለመሆኑ

የስሚ ስሚ በጥቅሉ የተዓማኒነት አደጋ ቢኖርበትም ከሌሎች ማስረጃዎች የበለጠ ተዓማኒ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ ስለሆነም በተቻለ መጠን ተዓማኒነት የሌላቸውን ማስረጃዎች በማስቀረትና ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ፍ/ቤቶች የስሚ ስሚ ልዩ ደንቦችን መሥርተዋል፡፡ በመሠረቱ የስሚ ስሚ ደንብ የተመሠረተው የበለጠ ትክክለኛነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉትን ግንኙነቶች በመለየት ነው፡፡ ለስሚ ስሚ ልዩ ድንጋጌ ሲቀመጥም ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች የፍርድ ቤት ውጤታማነት እና ፍትሐዊነት ናቸው፡፡ በመሆኑም የስሚ ስሚ ደንብ ግብ ዳኛው ተዓማኒነት የሌላቸውን ማስረጃዎች በመከልከል ዕውነትን የመፈለግ ሥራውን እንዲያሳካ ማገዝ ነው፡፡[80]

በ'ኮመን ሎው' የሕግ ሥርዓት የምስክርነት ማስረጃው በፍርድ ቤት ለተያዘውና ለአከራካሪው ኩነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመጀመሪያው ተናጋሪ በመሞቱ፣ የአዕምሮ ወይም የአካል ጉዳት ደርሶበት አሊያም በሌላ ምክንያት ፍርድ ቤት ቀርቦ ለመመስከር ያልቻለ እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት አለው፡፡ ከዚህም ሌላ እነዚህ የተለያዩ ድንጋጌዎች እውነቱን ለማሳየት ጠቃሚ በመሆናቸው ሕጉ ከደነገገ የስሚ ስሚ ማስረጃን መቀበል አለብን የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ በተጨማሪም የተሻለ ሌላ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ የስሚ ስሚ ማስረጃን መቀበሉ አግባብነት አለው የሚል ክርክር ይቀርባል፡፡[81]

የስሚ ስሚ ማስረጃ በ'ኮመን ሎው' ቅቡልነትን እንዲያገኝ የሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡ እነርሱም፣ (ሀ) የማስረጃው ተዓማኒነት፣ (ለ) ቀጥተኛ ማስረጃ ሊሰጥ የሚችለው ምስክር ፍ/ቤት ቀርቦ ለመመስከር የማይገኝ መሆን፣ (ሐ) ማስረጃው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት እ.ኤ.አ. በ2006 በተደነገገው የኒውዚላንድ የማስረጃ ደንብ ቁጥር 18(1) መሠረት የስሚ ስሚ መግለጫ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች መግለጫው ተዓማኒ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ ከሆነ፣ ተናጋሪው የማይገኝ ከሆነ፣ ወይም እንዲቀርብ ቢደረግ አላስፈላጊ ወጭንና የጉዳዩን መዘግየት እንደሚያስከትል ዳኛው ካመነ፣ የስሚ ስሚ ቅቡልነት አለው፡፡ ተናጋሪው የሌለ ነው የሚባለው ሰውየው ከሞተ፣ ከኒውዚላንድ ውጭ ከሄደና በምስክርነት የማቅረብ ምክንያታዊነት ከሌለ፣ (በዕድሜ፣ በአካል ወይም በአእምሮ) ለምስክርነት የማይበቃ ከሆነ፣ ተገቢ ፍለጋ ተደርጎ የማይታወቅ አሊያም የማይገኝ ከሆነ፣ ወይም ለመመስከር የማይገደድ ከሆነ ነው፡፡[82]

---

[79] *Ibid*, pp.15-6.

[80] *Ibid*, p. 18.

[81] Minelik Alemu, (1990), *Testimonial Evidence and Ethiopian Law* (A.A U.F.L, Unpublished), pp. 20-21.

[82] Don Mathias, (2006), *Observations on the Hearsay Provisions of the Evidence Act* [NZ], Accessed on 13/07/2012, p 4.

በአጭሩ በወንጀል ጉዳይ[83] የስሚ ስሚ ማስረጃ በ'ኮመን ሎው' በመርህ ደረጃ ቅቡልነት ባይኖረውም በባህርያቸው በስሚ ስሚ ማስረጃ ሥር የሚወድቁ ነገር ግን በይዘታቸው ምክንያት እውነትን[84] ያሳያሉ ተብለው የሚገመቱና በፍትሕ መንበራት ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ዓይነቶች አሉ። ዋና ዋናዎቹን ቅቡልነት ያላቸው የስሚ ስሚ ማስረጃዎች ከዚህ ቀጥለን እንመረምራለን።

## 4.3.1. ቀድሞ በተደረገ ክርክር ላይ የቀረበ ማስረጃ

በተከራካሪ ወገኖች መካከል ቀደም ሲል በተደረገ ክርክር ላይ ቀርቦ የነበረ ማስረጃ ያንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳት በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል። ማስረጃው ክርክሩ በተዘጋ፣ አሊያም በክርክር ላይ ባለ ወይም አሁን በተያዘ ጉዳይ ቀደም ሲል የቀረበ ሊሆን ይችላል። ክርክር የተደረገው በፍርድ ቤቶች ወይም በሌሎች የዳኝነት አካላት ፊት ሊሆን ይችላል።[85] ከዚህም ሌላ ጉዳዩ የወንጀል አሊያም የፍትሐብሔር ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

ይህ የምስክርነት ማስረጃ ቅቡልነት የሚያገኘው ምስክሮች እንደማይገኙና እንደገና የምስክርነት ማስረጃ ሊሰጡ እንደማይችሉ ሲረጋገጥ ነው። በመሆኑም ቀድሞ የተሰጠውን ማስረጃ ለማቅረብ የሚሻ ወገን ምስክሩ የት እንዳለ ለማወቅ ተገቢውን ፍለጋ አድርጎ ያልተሳካለት መሆኑንና ምስክሩ ፍርድ ቤት መቅረብ እንደማይችል ማስረዳት አለበት። ምስክሩ የመጀመሪያውን የምስክርነት ማስረጃ ከሰጠ በኋላ የአእምሮ መጓደል አሊያም የሰውነት ጤና ማጣት ሊያጋጥመው ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ምስክሩ ጤናው የተጓደለ መሆኑን በማስረዳት ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረን ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። ከዚህም ሌላ የቀድሞውና በአሁኑ ክርክር የተያዙት ነጥቦች ተመሳሳይ መሆን አለባቸው። ተከራካሪው ወገን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ ዕድል እንደነበረው ማረጋገጥ ከተቻለ ማስረጃው ቅቡልነት አለው።

## 4.3.2. በመደበኛ የንግድ ሥራ ላይ የተሰጡ መግለጫዎች

ይህ ልዩ ድንጋጌ ሙያዊ የንግድ ግዴታ በሚከወንበት ወቅት በጽሁፍ ሆነው በፊርማ የተረጋገጡ ሰነዶች ላይ የሚሰጡ መግለጫዎችን ይመለከታል። በገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ላይ የተቀመጡ መግለጫዎች ከስሚ ስሚ ማስረጃ መርህ በተለየ ሁኔታ በማስረጃነት ቅቡልነት አላቸው።[86] ምክንያቱም የመደበኛ የንግድ ሥራ መዛግብት በየጊዜው ክትትል ስለሚደረግላቸው ከሌሎች ማስረጃዎች የበለጠ ትክክለኛ ስለመሆናቸው እምነት ይጣልባቸዋል።[87]

"ንግድ" የሚለው ቃል አንድ ሰው ሙያው አድርጎ በመያዝ ሥጋዊ ፍላጎቱን ለማርካትና ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማሟላት ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚያከናውነውን ሥራ

---

[83] በአሁኑ ወቅት የስሚ ስሚ ማስረጃ በፍትሐብሔር ጉዳይ ቅቡልነት ያለው ማስረጃ ነው። See for example Raymond, **op cit** p. 140. According to him, hearsay evidence is now admissible in civil proceedings, but an exclusionary rule continues to operate against the admission of hearsay evidence in criminal trials.

[84] የስሚ ስሚ ልዩ ድንጋጌዎችን አስመልክቶ Paul C. Giannelli የተባለ ምሁር የሚከተለውን ጽፏል፡፡ "Hearsay exceptions are based on some circumstantial guarantee of truthworthiness that is thought to warrant admissibility notwithstanding the lack of cross-examination, oath, and personal appearance of the declarant". Paul C. Giannelli (2009), *Undestanding Evidence*, (3rd Edition), (Mattehew Bender & Co.), p. 76.

[85] Menilik, *supra* note 81, p. 25.

[86] *Ibid, p.* 22.

[87] S.C Sarkar, (1965), *Sarkar on Evidence* (11th Editioin), p. 305.

ያጠቃልላል፡፡[88] ቃሉ ሰፊ በመሆኑ አንድ ሰው ሙያዬ ብሎ የያዛቸውን (የተደጋጋሚነት ባህርይ ያላቸውን) ሥራዎች ሁሉ ይሸፍናል፡፡ ቃሉ አንዴ ብቻ የሚከናወኑ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የማስያዝና የንግድ ቤት የመሸጥ ወ.ዘ.ተ ሥራዎችን አያካትትም፡፡ ምክንያቱም እንደነዚህ ያሉት ሥራዎች ሙያዬ ተብለው የማይሠሩ ቀጣይነት የሌላቸውና ኑሮም በእነዚህ ሥራዎች ላይ የሚመሠረት ባለመሆኑ ነው፡፡[89]

በ'ኮመን ሎው' የሕግ ሥርዓት መሠረት መግለጫ ሰጭው ስለሥራው የመዘገበውን ጉዳይ ማወቅ አለበት፡፡ በተጨማሪም የተመዘገበውን ጉዳይ ሆነ ብሎ በሀሰት ለመመዝገብ የሚያነሳሳው ምክንያት መኖር የለበትም፡፡ ይህም እንዲሟላ የሚያስፈልገው ምስክሩ ስለ ጉዳዩ ግላዊ እውቀት እንዲኖረው ያስፈልጋል በሚለው መርህ መሠረት ነው፡፡ በሕንድ የማስረጃ ሕግ መሠረት የግል እውቀት አለመኖር ማስረጃውን ዋጋ ያሳጣዋል፡፡ የዚህ ዓይነቱ መዝገብ የምስክሮችን የማስታወስ ችሎታ ለመረዳት ያገለግላል፡፡ ከዚህም ሌላ መዛግብቱ በመዘገባቸው ሰው ጥቅም ላይ በማስረጃነት ያገለግላሉ፡፡[90]

የንግድ ሥራን የሚመለከቱ መግለጫዎች በልዩ ሁኔታ በማስረጃነት ቅቡልነትን እንዲያገኙ የሚከተሉት ነጥቦች [91] መሟላት አለባቸው፡፡ (1) መግለጫው ስለኩነቶች፣ ሁኔታዎች፣ አስተያቶች፣ የሚመለከት መሆን አለበት፤ (2) መግለጫው የተመዘገበው የንግድ ሥራው በተከናወነበት ሰዓት ወይም ወዲያውኑ ሊሆን ይገባል፤ (3) የተመዘገበው ስለንግዱ እውቀት ባለው ሰው ወይም ከዚህ ሰው መረጃ በመውሰድ መሆን ይኖርበታል፤ (4) መረጃው የተመዘገበው በአዘቦቱ በተለመደው ሁኔታ ስለተከናወነው የንግድ ሥራ እንዲሆን ይጠበቃል፤ (5) ምዝገባ ማከናወን በሥራው የተለመደ ተግባር መሆን አለበት፤ 6) የምዝገባ ሥራው በሕጉ መሠረት ሊከናወን ይገባል፤ (7) የመግለጫው ምንጭ፣ ወይም መግለጫው የተዘጋጀበት ሁኔታ የመግለጫውን እውነት ያለመሆን የሚያመለክት መሆን የለበትም፡፡

### 4.3.3. የሟች ሰው መግለጫ (Dying declaration)

የሟች ሰው መግለጫ አንድ ሰው በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ የሚናገረውን ቃል የሚመለከት ነው፡፡ መግለጫው የሰውየውን ሞት ምክንያት ወይም ድርጊት የሚያሳይ እስከሆነ ድረስ (ጉዳዩ የፍትሐብሔርም ሆነ የወንጀል) በስሚ ስሚ ማስረጃነት ተቀባይነት አለው፡፡[92] በሞቱና በሞቱ ምክንያት መካከል የጠበቀ ግንኙነት መኖር አለበት፡፡[93]

የሟችን ሞት ያስከተለው ድርጊት የሚለው ሀረግ የሰውየውን ሞት ካስከተሉ ነገሮች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሁኔታዎች ሁሉ የሚያካትት ሲሆን ሟች ሁኔታዎቹን የገለፃቸው የሞቱ ምክንያት ከመነሳቱ በፊት አሊያም በኂላ መሆኑ ግን ለውጥ የለውም፡፡[94] የሟች መግለጫ በማስረጃነት ቅቡልነት ይኖረው ዘንድ በሞት አፋፍ ላይ ያለው ሰው ነገሮችን የማስተዋል ችሎታ ሊኖረው ይገባል፤ መግለጫውንም በአስተውሎት የሰጠው መሆን አለበት፡፡ የሚሰጠው መግለጫ በስሚ ስሚ ላይ መመሥረትም የለበትም፡፡ ከዚህም ሌላ ሟች ፍርድ ቤት ቢቀርብ ኖሮ ለምስክርነት ብቁ መሆን አለበት፡፡[95] ይህ የሟች ሰው መግለጫ ቅቡልነትን እንዲያገኝ የሚደረገው መሞቱን ያወቀው ሰው ለሞቱ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ አይዋሽም

[88] *Ibid.*

[89] *Menilik, supra* note 81, p. 23.

[90] Sarkar, *supra* note 87.

[91] See Giannelli, *supra* note 84, p. 78.

[92] *Ibid*, *p*. 21.

[93] Sarkar, *supra* note 87, p. 354.

[94] ታደለ፣ በቁጥር 14 የተጠቀሰ፤ ገጽ 37

[95] ዝኒ ከማሁ

ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡[96] በሞት አፋፍ ላይ ያለ ሰው ሀሰት በመናገር ኃጢያት ለመጨመር አይፈልግም የሚል እምነት አለ፡፡ ይልቁንም ኃጢያቱን መናዘዝና እውነቱን መናገር እንደሚፈልግና ለሞቱ ያበቃውንም ምክንያት በሚመለከት እንደማይዋሽ ይገመታል፡፡

# 5. የስሚ ስሚ ማስረጃ በ'ሲቪል ሎው'

## 5.1. የ'ሲቪል ሎው' ልዩ ባህርያትና የስሚ ስሚ ማስረጃ ሚና

በ'ሲቪል ሎው' የሕግ ሥርዓት "የስሚ ስሚ ደንብ" ስለሌለ የስሚ ስሚ ማስረጃ በመሠረቱ ቅቡልነት አለው፡፡ ለምሳሌ፣ በስኮትላንድ የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት አለው፡፡[97] ይሁን እንጂ በ'ሲቪል ሎው' የሕግ ሥርዓት ስለስሚ ስሚ ማስረጃ የተደነገገም ሆነ የተዓፈ ነገር ማግኘት ያስቸግራል፡፡ ማስረጃ በምን ሁኔታ መሰብሰብ እንዳለበት ወይም አንድ ነገር በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችለው ምን ምን ሁኔታዎችን ሲያሟላ እንደሆነ የሚደነግግም የማስረጃ ደንብ የለም፡፡ ይህም የሆነው የሚቀርብለትን ማስረጃ በሚገባ የመመርመርና እውነትን የማውጣት ግዴታ ያለበት ዳኛ ገለልተኛና በሕግ እውቀትና ልምድ ያለው ባለሙያ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም፣ በወንጀል ጉዳይ ዳኛው በማናቸውም መንገድ ኩነቱን ለማረጋገጥ የሚችልን ማስረጃ ይቀበላል፡፡ ተከሳሹም ማስረጃን በፍርድ ቤት ውስጥ የመመርመርና ስለማስረጃው የመወያየት ዕድል አለው፡፡ ስለሆነም የስሚ ስሚ ማስረጃ በማስረጃነት ከቀረበ ቅቡልነት እንዳለው ፀሀፍት ያምናሉ፡፡[98] በጥቅል አነጋገር በዘመናዊ 'ሲቪል ሎው' አገሮች ማስረጃ የማግለል ደንብ (exclusionary rule) ተቀባይነት ስለሌለው የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት አለው፡፡[99]

በጀርመንና በፈረንሳይ የማስረጃ ቅቡልነት ደንቦች ላላ ያሉ ወይም ከነጭራሹ የሉም ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት በምክንያትነት ይቀርባሉ፡፡ በቅድሚያ ማስረጃ የመስማት ሂደት ለሕዝብ ግልጽ መሆኑ ነው፡፡ በአንድ መዝገብ ውስጥ የተካተቱትን ማስረጃዎች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ መመርመሩ ይዘታቸውን የማረጋገጫ ዘዴ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በእነዚህ አገሮች የስሚ ስሚ ማስረጃ በመሠረቱ ቅቡልነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ምስክሮች የሚጠሩትና የሚጠየቁት በፍ/ቤት እንጅ በአንደኛው ተከራካሪ ወገን ባለመሆኑ ላንዱ ወገን የሚያደሉበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሆኑም ምስክርነታቸው ቢያንስ አድሎአዊነቱ ወይም ወገንተኛነቱ "አናሳ" ስለሚሆን፣ የስሚ ስሚን ለፍ/ቤቱ ሪፖርት ሲያደርጉም ተዓማኒነቱ የበለጠ ይሆናል፡፡

ምስክሩ የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ የተቆራረጠ ሳይሆን ፍሰቱን ጠብቆ ነው፤ ፍ/ቤቱ ለሚጠይቀው ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ በተከራካሪው ወገን ተቃውሞ የማይቀርብበትና ፍሰቱም የማይቋረጥ ስለሆነ በስሚ ስሚ ደንብ መሠረት ቅቡልነት የሌለው ማስረጃ ጭምር በሕዝብ ፊት ለፍ/ቤት እንዲነገር ያስችላል፡፡ ፍ/ቤቱም ምስክሩን ቃል እንደወረደ ቃል በቃል ሳይሆን ዋና ዋና ነጥቦችን በማጠቃለል ይመዘግባል፡፡ ከዚያም የስሚስሚ ማስረጃውን ከቀጥተኛ ማስረጃ ጋር በማነጻጸር ዳኛው ተገቢ ነው የሚለውን ክብደት ይሰጠዋል፡፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው ምክንያት በርካታ ተችዎች እንደሚስማሙበት በ'ሲቪል ሎው' ሕግ ሥርዓት እንደ 'ኮመን ሎው' 'ጁሪ' (የኩነት ዳኝነት አካል) ባለመኖሩ የስሚ ስሚ ምስክርነት ደንቦች ላላ እንዲሉ

[96] ዝኒ ከማሁ

[97] Alistair, Rosalind and Bruce (2000), *SCOTS LAW for Journalists* (7th ed)

[98] Jean-Marc Baisus, (2002), *Common V. Continenetal, A reaction to Mr. Evan Whitton's 1998 Murdoch Law School Adress,* p. 12.

[99] Jeremy A. Blumenthal (2001), "Shedding Some Light on Calls for Hearsay Reform: Civil Law Hearsay Rules in Historical and Modern Perspective", 13 *Pace Int,l L.Rev.* 93 Avalable at: <http://digitalcommons.pace.edu/vol13/iss1/3> Accessed on 11/08/12, p. 94.

ተደርጓል፡፡ በ'ኮመን ሎው' የስሚ ስሚ ደንብ የተፈጠረው የሕግ ባለሙያ ያልሆኑትን 'ጁረሮች' (የኩነት ዳኞች) የማይታመን ወይም አግባብነት የሌለውን ማስረጃ በሚመለከት እንዳይወናበዱ ለመርዳት ሲሆን፣ 'ጁሪ' በሌለበት የ'ሲቪል ሎው' በማስረጃው ግራ የሚጋባ ባለመኖሩ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት አለው የሚል አስተሳሰብ ሲኖር ማስረጃውን የመመዘኑ ኃላፊነትም በሕግ ምሁር በሆነው በዳኛ ትከሻ ላይ ይወድቃል፡፡[100]

## 5.2. በ'ሲቪል ሎው' የስሚ ስሚ ቅቡልነት የሚያጣባቸው ሆኔታዎች

በጥቅሉ የ'ሲቪል ሎው' ተከታይ ሀገሮች የስሚ ስሚን ለመከልከል እንደ 'ኮመን ሎው' ሰፊ፣ ዝርዝርና ውስብስብ የማስረጃ ደንቦች የሏቸውም፡፡ ይህ ማለት ግን የስሚ ስሚ ማስረጃ በ'ሲቪል ሎው' ሙሉ በሙሉ ያለምንም ገደብ ቅቡልነት አለው ማለት አይደለም፡፡ የኢጣሊያ የወንጀል ሕግ የስሚ ስሚን በግልጽ ይከለክላል፡፡ በተጨማሪም ሆላንድና ሀንጋሪ የስሚ ስሚ ማስረጃን ውድቅ ስለማደረጋቸው የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ የጀርመን ፍ/ቤቶች ማናቸውንም አግባብነት ያለው ማስረጃ የሚቀበሉና የሚመረምሩ ሲሆን፣ የስሚ ስሚንም ይቀበላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤት ያልቀረበ ሰው ቀደም ሲል የሰጠው የምስክርነት ቃል ቢኖርም ፍ/ቤት ፊት ቀርቦ እንዲመረመር ያደርጋሉ፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃን በተመለከተ ደንቡ የሚሠራው በጽሁፍ በተደረጉ ማስረጃዎች ላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ በፈረንሳይ በፍትሐብሔር ጉዳዮች የቃል የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት አለው፤ የወንጀል ሥነሥርዓት ሕጉ ግን ጥቂት ገደቦችን አስቀምጧል፡፡ በጥቅሉ በ'ሲቪል ሎው' የስሚ ስሚ ማስረጃ እንደወረደ ሙሉ በሙሉ ቅቡልነት አለው ባይባልም በመርህ ደረጃ ግን ቅቡልነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡[101]

በ'ሲቪል ሎው' ነፃ የማስረጃ ምዘና መርህ ገቢራዊ ስለሚደረግ (የስሚ ስሚንም ጨምሮ) ማናቸውም አግባብነት ያለው ማስረጃ ቅቡልነት አለው፡፡ ይህም መርህ እያንዳንዱ ጉዳይ የራሱ የሆነ ባሕሪ ያለውና ከሌላው የተለየ መሆኑን ይቀበላል፣ ለዚህም አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ይፈቅዳል፡፡ ማናቸውም በምርመራ ተፈልጎ የተገኘ ጥሩ (የስሚ ስሚም ሆነ ሌላ) ማስረጃ ፍ/ቤት ቀርቦ በሕዝብ ፊት መመርመር አለበት የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡[102]

በጀርመን ሥራ ላይ ከዋሉት መርሆዎች አንዱ ማስረጃ በቃል ፍ/ቤት ፊት መቅረብ አለበት የሚል ነው፡፡ በዚህ መርህ መሠረት ለውሳኔው መሠረት የሚሆኑ ማስረጃዎች በቃል ፍ/ቤት ፊት መቅረብ ያለባቸው ሲሆን ይህም የቃል ክርክር እንዲኖር ያስገድዳል፡፡ ይህም በበኩሉ በጀርመን ሕግ የፍርድ ሥራ በግልጽ ችሎት በሕዝብ ፊት እንዲደረግ የሚያደርግ፣ ማለትም ታዳሚው የጉዳዩን አመራርና የማስረጃውን አቀራረብና አመዛዘን የሚያይበትና የሚታዘብበት የፍ/ቤት ሥራ ከሕዝብ እይታ ውጭ የማይከናወን መሆኑን የሚያረጋግጥ መርህ ነው፡፡ በመሆኑም የቀረቡ የሠነድ ማስረጃዎች ይዘት በሕዝብ ፊት መቅረብ ያለባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ መርሁ ከሠነድ ማስረጃ ይልቅ ለሰው ማስረጃ ክብደት ይሰጣል የሚሉ አሉ፡፡[103]

በ'ሲቪል ሎው' ዳኛው (የኩነት ዳኛ ሳይሆን) ሕግ የተማረ በመሆኑ አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ቅቡልነት የሌላቸውን ማስረጃዎች ውድቅ ያደርጋል የሚል ግምትና በእርሱም ላይ

---

[100] ዝኒ ከማሁ

[101] Blumenthal, *supra* note 99, p. 100.

[102] *Ibid*, p. 190.

[103] It was interpreted as the precedence of personal evidence (witnesses, experts) over documentary evidence and this related to the "best evidence rule". Michael Bahlander "Basic Concepts of German Criminal Procedure- An Introduction" *Durham Law Review online* vol. 1. Accessed on 11/08/2012, p. 20-1.

እምነት ተጥሏል፡፡ ለዚህም ነው የማስረጃ ደንቦች ላላ ያሉ እንዲሆኑ የተደረገው፡፡[104] ሌላው ምክንያት ጉዳዮችን ለመስማት ዳኞችና ገምጋሚዎች (assessors) በጋራ እንዲሠሩ መደረጉ ነው፡፡ በአንፃሩ በ'ኮመን ሎው' 'ጁረር' (juror) የተባሉት ባለሙያ ያልሆኑ ሰዎች እንዲሠሩና የማስረጃ ሕግም ውስብስብና ሰፊ እንዲሆን ያደረገው ስለመሆኑ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ሆኖም ግን በ'ሲቪል ሎው' የገምጋሚዎች መኖር ከ'ጁሪ' ጋር ሲነጻጸር ሁለት ልዩነቶችን እናጤናለን፡፡ እነርሱም (ሀ) በጀርመንና በመጠኑም ቢሆን በኢጣሊያ እነዚህ ገምጋሚዎች በከፊል ባለሙያ ናቸው፡፡ ገምጋሚዎች በሥራቸው ላይ ለረጅም ጊዜ የቆዩ በመሆናቸው በርካታ ጉዳዮችን የማየት ዕድል አላቸው (ይህ ከሞላ ጎደል በ'ኮመን ሎው' 'ግራንድ ጁሪ' ከሚባለው ጋር ይመሳሰላል)፡፡ በዚህም የተነሳ ከ'ኮመን ሎው' 'ጁሪ' የበለጠ ጉዳዮችን የመመልከትና የስሚ ስሚ ማስረጃን በአግባቡ መለየትና መመዘንን ከተግባር ይማራሉ፡፡ በተጨማሪም አብረዋቸው የሚቀመጡት ዳኞች ስለስሚ ስሚ አደጋዎች ገለጻ ያደርጉላቸዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ የጁሪ ወይም የገምጋሚዎች መኖር ያለመኖር ለስሚ ስሚ ደንብ ዋና ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡[105]

በ'ሲቪል ሎው' ከወገናዊነት የፀዳ እውነትን የማፈላለግ ፍልስፍና አለ፡፡ በ'ኮመን ሎው' ዋናው ነገር ተከራካሪ ወገኖች የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ደንቦችን ተከትለው ክርክራቸውን ከማድረጋቸው ላይ ነው፡፡ ይህም እውነትን አንጥሮ ከማውጣት ይልቅ ፍሬ ነገሮች ላይ በማተኮር ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አሸናፊውን ወደመለየቱ ያዘነብላል፡፡ በ'ሲቪል ሎው' ግን ትኩረት የሚሰጠው በትክክል ምን እንደተፈጸመ ለይቶ ለማወቅ ስለሆነ፣ መርማሪ ዳኛው እውነትን አንጥሮ በማውጣቱ ሂደት የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡ እውነትን አንጥሮ ለማውጣት ደግሞ (የስሚ ስሚን ጨምሮ) ማናቸውንም ማስረጃ መቀበልና መመርመርን ግድ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ውስብስብ በሆኑ የማስረጃ ደንቦች መታጠር ዕውነትን አንጥሮ ለማውጣት እንደእንቅፋት ሊቆጠር ይችላል፡፡[106]

ሦስተኛው ነጥብ ተቋማዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡ በ'ሲቪል ሎው' ፍ/ቤቱ በማስረጃ ጉዳይ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣ በክስ መስማት ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ምን እንደሚጠየቅ የሚያውቁ ከሆነ፣ ማናቸውም ቢሆን ሌላውን ወገን ለማስደንገጥ ዕድል የለውም፡፡ ለማሸነፍ በማሰብም የተገኘውን ጥበብ ለመጠቀምም የሚያነሳሳ ነገር የለም፡፡ ምስክሮችም ላንደኛው ተከራካሪ የመወገን ዕድላቸው አነስተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ላንዱ ወገን የሚያዳላ ምስክር የመሆን ዕድሉ በእጅጉ የሚቀንስ በመሆኑ የስሚ ስሚም ቢሆን ሊቀርብ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከተከራካሪዎቹ ይልቅ ፍ/ቤቱ ምስክሮችን የመምረጥ ኃላፊነት አለበት፡፡[107]

በሌላ በኩል ከተከራካሪዎቹ ይልቅ ፍ/ቤቱ ክርክሩ ከመሰማቱ በፊት ማስረጃ የመሰብሰብ ኃላፊነት አለበት፡፡ በ'ኮመን ሎው' ግን ማስረጃ የመሰብሰብ ኃላፊነት የሚወድቀው በተከራካሪ ወገኖች ትከሻ ላይ ነው፡፡ ይህም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ምስክር የማምጣት በርን ይከፍታል፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ ሲቀርብ የኩነት ዳኞቹ በክሱ ሂደት ዋናውን ተናጋሪ ፈልጎ የማግኘት ዕድል አላቸው፡፡ የዋናው ተናጋሪ ቃል ከስሚ ስሚ ምስክሩ ከተለየም ሁለቱንም ፍ/ቤት አስቀርቦ መመርመርና ተዓማኒነታቸውን መመዘን ይቻላል፡፡ ዋናው ተናጋሪ በማይገኝበት ጊዜ ከፍ/ቤት ውጭ የተሰጠውን መግለጫ ትክክለኛነት በሚመለከት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በሚሰማበት ጊዜ መረጃ ለማሰባሰብ ዕድል አለው፡፡[108] በመሆኑም በክስ ወቅትም ሆነ ከዚያ በፊት በተከራካሪ ወገኖች የሚሰበሰብ ማስረጃን ማስወገድ ዳኛውን ማናቸውንም አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች

[104] Blumenthal, *supra* note 99, p. 190.

[105] *Ibid*, pp. 110-11.

[106] *Ibid*, p. 112.

[107] *Ibid*, p. 113.

[108] Damaska in Blumenthal, *supra* note 99, p. 114.

ለመመርመር፣ ለመመዘንና እያንዳንዷን ማስረጃ እርስ በርሷ ለማገናዘብ ያስቸግረዋል፡፡ እናም የስሚ ስሚ ምንም ጠቀሜታ አይኖረውም፡፡[109]

በርግጥ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በሁለቱም የሕግ ሥርዓቶች አሉ፡፡ በ'ሲቪል ሎው' ግን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ማስረጃ ይመረምራል፤ የኩነትና የሕግ ጉዳይን ይመለከታል፤ አስፈላጊም ከሆነ (ከ'ኮመን ሎው' በተለየ ሁኔታ) የስሚ ስሚ ማስረጃን ተቀብሎ ይመረምራል፡፡ 'ሲቪል ሎው' ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ምክንያት ማስቀመጥ አለበት፡፡ በመሆኑም  በሕጉና በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ ምክንያቱን ዘርዝር አድርጎ መግለፅ ይጠበቅበታል፤ ለምን የስሚ ስሚ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ እንደሰጠም ምክንያቱን ማሳየት አለበት፡፡ በጥቅሉ እነዚህ ከላይ የተመለከትነው እውነትን አንጥሮ የማውጣት አስተሳሰብ፣ ተቋማዊ ሁኔታና በዳኞች ላይ እገዛዊ ቁጥጥር ማድረግን አጠቃሎ ይይዛል፡፡ እነዚህ ተቋማዊና ንድፈ ሀሳባዊ ጉዳዮች የስሚ ስሚን በሚመለከት ላላ ያለ ደንብ እንዲኖር ወሳኝ ነገሮች ከመሆናቸውም በላይ በ'ሲቪል ሎው' የማስረጃ ቅቡልነት ከ'ኮመን ሎው' የተለየ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ [110]

# 6. የስሚ ስሚ ማስረጃ በኢትዮጵያ

## 6.1. የማስረጃ አሰባሰብና የስሚ ስሚ ሚና በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ከተመሠረተባቸው መርሆዎችና ስትራተጂዎች አንዱ ንጹሀንን ከአጥፊዎች በአግባቡ መለየት ነው፡፡[111] ይህ ሊደረግ የሚችለው ደግሞ በማስረጃ አማካኝነት ሲሆን በማስረጃ አሰባሰብና አያያዝ ረገድ የፌዴራልና የክልል የፍትሕ አካላትን አቅም መገንባት እንደሚያስፈልግ ፖሊሲው ይገልፃል፡፡ የግንባር ቀደምትነት ኃላፊነቱም በፍትሕ ሚ/ር ትከሻ ላይ ወድቋል፡፡[112]

የፍትሕ አካላት ማለትም ፍ/ቤት፣ ዐቃቤ ሕግና መርማሪ ፖሊስ በማስረጃ አሰባሰብ ሂደት እንደሚሳተፉ ፖሊሲው ያመላክታል፡፡ በኢትዮጵያ የማስረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ውስጥ ፍ/ቤት ሚና ያለው ሲሆን፣ በወ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 143 እንደተደነገገው "ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት [ተጨማሪ ማስረጃ] አስፈላጊ ከመሰለው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ምስክር መጥራት ይችላል፡፡"[113] ይህም የ'ሲቪል ሎው'ን የማስረጃ አሰባሰብ

[109] Blumenthal, *supra* note 99, p. 113.

[110] *Ibid*, p. 115

[111] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የካቲት 25/2003 ዓ.ም. ቁጥር 1.4.ረን ይመልከቱ፡፡

[112] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 2.6ን ይመልከቱ፡፡

[113] የድንጋጌው ርዕስ "ተጨማሪ ምስክሮች" ስለሚል ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቅርብ ለማዘዝ የሚያስችለው ድንጋጌ ነው በማለት መተርጎም ይቻላል፡፡ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 143ን ይመልከቱ፡፡የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤትም ተመሳሳይ ሥልጣን አለው፡፡ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 87ን ይመልከቱ፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይም ተመሳሳይ ድንጋጌ ያለ ሲሆን ፍ/ቤቱ  ተጨማሪ  ምስክርና የሠነድ ማስረጃ እንዲቀርብ የማዘዝ ሥላጣን አለው፡፡ ይህን የሚመለከተው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 264 እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

1) "በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ነገሩን ሚያውቅ ወይም ለክርከሩ ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍ በእጁ የሚገኝ ሰው ፍርድ ቤት በሚገኝበት ጊዜ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም በእጁ የሚገኘውን ጽሑፍ  እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡
2) እንዲሁም ተከራካሪዎቹ ወገኖች ካቀረቡዋቸው ምስክሮችና ከራሳቸው በቀር ሌሎች ምስክሮች መስማት ጠቃሚ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከገመተው፤ በሚወስነው ቀነ ቀጠሮ ተጠርተው

ሥርዓት የተከተለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤት ማስረጃ መሰብሰብ ያለበት በሕግ መሠረት መሆን እንዳለበትና በሕገወጥ መንገድ የተሰበሰበ ማስረጃ ቅቡልነት እንደማይኖረው አግባብነት ባላቸው ሕጎች እንዲደነገግ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያስቀምጣል፡፡[114]

ሌላው የ'ሲቪል ሎው' የማስረጃ ሥርዓት ልዩ ባሕርይ በሕዝብ ፊት ማስቻል (ግልጽ ችሎት) መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ሕገመንግሥት ይህንን መርህ አካቶ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም በወንጀል "የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት *ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው*፡...."[115] (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ይህም ከላይ ስለ 'ሲቪል ሎው' የማስረጃ ሁኔታ እንደተመለከትነው ፍትሕን ለሕዝብ እይታ ግልጽ በማድረግ ፍትሕ ሲሰጥ ሕዝቡ እንዲታደምና እንዲታዘብ ዕድል ይሰጣል፡፡ ሆኖም ግን ይህ መብት ፍፁማዊ አይደለም፤ ገደብ አለው፡፡ በሕገመንግሥቱ እንደተቀመጠው፣ "...የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡"[116] የሕገመንግሥቱ ድንጋጌ በግልጽ እንዳስቀመጠው በግልጽ ችሎት የመሰማት መብት ሊገደብ የሚችለው ሦስት ጥቅሞችን ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡ እነርሱም፣ የተከሳሹን የግል ሕይወት፣ የኢትዮጵያን ደህንነት እና የሕዝብን ሞራል ለመጠበቅ የሚደረጉ ገደቦች ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ በመብቱ ላይ ገደብ ሊደረግ አይቻልም፡፡ ይህም ገደብ ከላይ ከተመለከትነው የ'ሲቪል ሎው' ገደብ ብዙም የተለየ አይደለም፡፡

ተከሳሾች "ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡"[117] ውሳኔ የሚሰጠው ፍ/ቤትም ማስረጃውን የተቀበለበትንና ያልተቀበለበትን ምክንያት፣ እንዲሁም ለውሳኔው መሠረት ያደረገውን ሕግ በመጥቀስ ምክንታውን (reasoning) ማስቀመጥ አለበት፡፡[118] ይህ የሚያሳየው የይግባኝ መብት እውነትን አንጥሮ የማውጣት ዓላማ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የፍትሐብሔርና የወንጀል ሥነሥርዓት ሕግጋትም እውነትን አንጥሮ ለማውጣቱ ዓላማ ተመሳሳይ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 143 ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ የሚሰጠው ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከላይ የተመለከትናቸው ሦስት ነጥቦች ማለትም የፍርድ ቤት ማስረጃ የማሰባሰብ ሥልጣን፣ ክርክር በሕዝብ ፊት በግልጽ ችሎት እንዲታይ ማድረግ፣ እና እውነትን አንጥሮ የማውጣት ሁኔታ ባንድ ላይ ሲታዩ የኢትዮጵያ የማስረጃ ሕግ ከ'ሲቪልሎው' ጋር እንደሚመሳሰል እንገነዘባለን፡፡

ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጡ ማስረጃዎች በማስረጃነት ሊቀርቡ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ይኸውም "ምስክሩ የሞተ እንደሆነ ወይም የአእምሮ ጉድለት ያገኘው እንደሆነ፣ ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ፣ በህመም ምክንያት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለመኖሩ ፍ/ቤት መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት የሰጠው ቃል ተነቦ በማስረጃነት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይቀርባል፡፡"[119] ይህ ድንጋጌ ከፍ/ቤት ውጭ የተሰጡ ማስረጃዎች ክርክሩ በሚሰማበት

---

የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ወይም በእጃቸው የሚገኘውን ጽሑፍ እንዲያቀርቡ የመጥሪያ ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡"

[114] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የካቲት 25/2003 ዓ.ም. ቁጥር 3.16.1ን ይመልከቱ፡፡

[115] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 20 (1)፡፡

[116] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 20 (1) ሁለተኛውን ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ፡፡

[117] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 20 (6)

[118] የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 149 (1)ን ይመልከቱ፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 182 (1) መሠረትም ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና ተወሰነበት ምክንያት መጻፍ አለበት፡፡

[119] የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/144፡፡ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች በከባድ የግፍ አገዳደል ወይም በከባድ የወንበዴነት ሥራን ብቻ የሚመለከቱ በመሆናቸው የድንጋጌው ገቢራዊነት በእጅጉ ውስን ነው፡፡ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 80ን ይመልቱ፡፡ (አሁን ግን ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት ሚቀርቡ

ጊዜ ፍ/ቤት ሊቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታዎች የሚገልፅ በመሆኑ በ'ኮመን ሎው' ከሚሠራበት የስሚ ስሚ መርህ ማለትም የምስክሩ ያለመገኘት መርህ ጋር ይመሳሰላል የሚል ግምት ይሰጣል። በሌላ አነጋገር ይህ ድንጋጌ የስሚ ስሚ መርህ ገቢራዊ ሲደረግ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ያስቀመጠ ሊመስል ይችላል።

ሆኖም ግን መሠረታዊ ልዩነት መኖሩ መዘንጋት የለበትም፤ በኢትዮጵያ ምስክሩ ያልተገኘ እንደሆነ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት የሰጠው የምስክርነት ቃል በመሆኑ ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት በማይቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም። ስለዚህ በ'ኮመን ሎው' ከሚሠራበት መርህ የተለየ ነው፤ ይልቁንም የሚመሳሰለው በ'ሲቪል ሎው' ፍ/ቤት በማስረጃ አሰባሰብ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ከሚሆንበት ሁኔታ ጋር ነው። በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 88 እንደተደነገገው ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍ/ቤት ማስረጃውን በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 147 ድንጋጌ መሠረት መመዝገብ ያለበት ሲሆን የኋለኛው ድንጋጌ የምስክርነት ማስረጃ መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦበት እንዲመዘገብ ያዛል።

## 6.2. ማስረጃን የመጋፈጥ መብት በኢትዮጵያ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 20(4) እንደተደነገገው የተከሰሱ ሰዎች "የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ… መብት አላቸው።" ይህ ድንጋጌ ማስረጃን የመጋፈጥ መብትን ያካተተ ነው። ድንጋጌው ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከትን የተከሳሾች መብት ያረጋግጣል። ተከራካሪ ወገን የቀረቡበትን ምስክሮች ሊጠይቅ የሚችለው በመስቀለኛ ጥያቄ ነው። መስቀለኛ ጥያቄ "በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ውስጥ ያለውን የስህተት ቃል፤ የሚያጠራጥር ቃል ወይም እውነት ያልሆነውን ቃል ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽና ለማስተባበል የሚደረግ ጥያቄ ነው።"[120] የስሚ ስሚ ማስረጃ ከቀረበ ምስክሮችን የመመርመርና ማስረጃውን የመመልከትን መብት ገቢራዊ ለማድረግ ያስቸግራል። በመሆኑም ሕገ-መንግሥቱ የስሚ ስሚ ማስረጃን ይከለክላል ለማለት ይቻላል።

በተጨማሪም የወንጀል ክርክርና የክስ መሰማት ሂደት ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ እንዲሆን ማስረጃን የመግለጽ ወይም የማስታወቅ ግዴታ እንዲኖር የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ይገልፃል። በዚህም መሠረት ዐቃቤ ሕግ የክስ መሰማት ሂደት ከመጀመሩ በፊት ለተከሳሹ የክስ መከላከያ ሊሆን የሚችለውን ጨምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ክሱን ለማስረዳት የተሰበሰበውን ማናቸውንም ማስረጃ ለተከሳሽ የመግለጽ ግዴታ እንዳለበት ተገልጧል። በወንጀል ፍትሕ መንግሥት ለተከሳሹ ጭምር የሚጠቅመውን ማስረጃ የሚሰብሰብ መሆኑ የ'ሲቪል ሎው' መሠረታዊ ባሕርይ ሲሆን ይህም እውነትን አንጥሮ ለማውጣት ይረዳል።

ከዚህም ሌላ በዐቃቤ ሕግ የሚገለጸው ማስረጃ ተከሳሹ የቀረበበትን ማስረጃ የመመልከትና የቀረበበትን ምስክር የመጠየቅ መብቱን ለማረጋገጥ ማስቻል እንዳለበት በፖሊሲው ላይ በግልጽ ተቀምጧል።[121] ይህም ማስረጃን የመጋፈጥ መብትን እንደሚመለከት ግልጽ ነው። መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብትን በማስጠበቅ ማስረጃን የመጋፈጥ መብትን ለመተግበር ደግሞ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት ሊኖረው አይገባም። የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ማስረጃን የመጋፈጥ መብት ሊገደብ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ሲዘረዝር፣ ማስረጃን መግለፁ ወንጀል ለመፈጸም የሚያስችል ከሆነ፣ የፍትሕ መጨንገፍን የሚያስከትል ከሆነ፣ ማስረጃው የሀገር መከላከያን፣ ፀጥታንና የሀገር ደህንነትን እንዲሁም ዓለማቀፋዊ ግንኙነቶችን የሚመለከት ከሆነ፣ ምስጢር

ጉዳዮች በርከት እንዲሉ ተደርጓል።የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የካቲት 25/2003 ዓ.ም. ቁጥር 3.18ን ይመልከቱ።) ቀደም ሲል ሕጉ ከተደነገገ ጊዜ ጀምሮ አንድም ጊዜ ለቀዳሚ ምርመራ የቀረበ ጉዳይ ስለአለመኖሩ ከሠላሣ ዓመት በላይ በፍትሕ ሚኒስቴር በሕግ ባለሙያነት የሠሩት አቶ ታዬ ንጋቱ በአንድ ወቅት ጸሐፊውን አጫውተውታል።

[120] የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 137(3) ን ይመልከቱ።

[121] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ ዝኒከማሁ፣ ቁጥር 4.5.2

ከሆነ፣ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ወይም የፋይናንስ ጥቅሞች ለማስጠበቅ የተፈለገ ምስጢር ከሆነ ገደብ ሊደረግ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡ ይህ ዝርዝር በልዩ ሁኔታ የስሚ ስሚ ማስረጃን ቅቡል ለማድረግ ሌሎች ሀገሮች ካስቀመጡት የተለየ ነው፡፡ ገደቡ የስሚ ስሚ ማስረጃን ቅቡል ለማድረግ ሳይሆን ከነጭራሹ ለማግለል የተፈለገና ሌሎች ሀገራዊ እሴቶችን ለማስጠበቅ የተፈለገ ይመስላል፡፡

በኩልማኒት አድሪያኖ እና ገብረ መድህን በኩረ መካከል የመኪና ሞተር ጥገናን በሚመለከት በተነሳ ክርክር[122] ላይ ባለሙያዎች የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ባለሙያዎች አስተያየት የሰጡት የመኪናውን ሞተር የጠረበውን ወይም የፈታውንና የገጠመውን ሰው በመጠየቅ ካገኙትና ከሰሙት ተነስተው ነው፡፡ ይህን ማስረጃ በሚመለከት የጠቅላይ ፍርድ ቤት፦

> ሰዎቹ ተጠርተው መልስም ሆነ ማብራሪያ የሰጡት ከባለሙያዎቹ ለቀረበላቸው ጥየቄ ነው፡፡ ይህም የተደረገው ግራ ቀኙ በሌሉበትና በሕግ በተፈቀደው መሠረት ጥያቄ ለማቅረብ በተሰጣቸው መብት ሳይጠቀሙ ብቻ ሳይሆን ምስክር ሆነው የቀረቡት ሰዎችም እውነት ለመናገር ማረጋገጫ ሳይሰጡ ነው፡፡

በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም እንደምንረዳው ማስረጃ በተከራካሪ ወገኖች ፊት ቀርቦ ሊመመረመርና በመስቀለኛ ጥያቄ አማካይነት ሊፈተሽ እንደሚገባ ነው፡፡

በአንድ የግድያ ወንጀል[123] ላይ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ካቀረባቸው ማስረጃዎች አንዱ ፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ የምስክር  ቃል ነው፡፡ ይህን ማስረጃ በሚመለከት የቀድሞው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፍርድ ቤት ‹‹… ያልቀረበው ምስክር ፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል… መስቀለኛ ጥያቄ ሊቀርብበት ያልቻለ ወይም በቃለ መሐላ ሥር ሆኖ ፍርድ ቤት እንኳ ያልተሰጠ በመሆኑ በማስረጃነት መቅረቡ ትክክል አልበነረም፤…›› የሚል ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው የክርክር ዘውግ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ደግሞ የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌም ቢሆን የስሚ ስሚ ማስረጃን በማስረጃነት ሳለመቀበል በግልጽ ያልከለከለ ስለሆነ የስሚ ስሚ ማስረጃ መቀበልን በመደገፍ ክርክር ለማቅረብ ይቻላል፡፡ የቀረበው ስሚ ስሚ እንኳ ቢሆን ማስረጃውን በመቀበል ተከራረካሪ ወገኖች እንዲመረምሩት በማድረግ በህሊና ሚዛን ላይ በማስቀመጥ አሳማኝ ካልሆነና ሚዛን የማይደፋ ሆኖ ከተገኘ በሱ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ መስጠት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ማስረጃውን የመመዘን ጉዳይ ለዳኞች የተተወ እንጂ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት የተከለከለ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ስለማስረጃ ቅቡልነት የተደነገገ የማስረጃ ደንብ ኢትዮጵያ የላትም የሚል ክርክር ሊቀርብ ይችላል፡፡ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 20(4)ም ቢሆን በወንጀል የተከሰሱ ሰዎችን መብት የሚመለከት በመሆኑ በፍትሐብሔር ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ስለዚህ የስሚ ስሚ ማስረጃ በፍትሐብሔር ጉዳይ ቅቡልነት አለው የሚል የክርክር ነጥብ ማንሳት ይቻላል፡፡

በ‘ኮመን ሎው’ የሕግ ሥርዓት ተከታይ በሆኑት ሀገሮች የስሚ ስሚ ማስረጃ በመርህ ደረጃ ቅቡልነት የሌለው በወንጀል ጉዳይ እንጂ በፍትሐብሔር ጉዳይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝና በዌልስ በፍትሐብሔር ጉዳይ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት አለው፡፡[124] በመሆኑም የስሚ ስሚ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ እንጂ በፍትሐብሔር ጉዳይ ቅቡልት ያለው ማስረጃ ነው[125] የሚለውን ንጽጽር ማንሳት ይቻላል፡፡

---

[122] ኩልማኒት አድሪያኖ v. ገብረ መድህን በኩረ፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 201/77 የፍርዶች መጽሐፍ፣

[123] ዐቃቤ ሕግ v. በዳዳ ወልዱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የ/ይ/መ/ቁጥር 734/79 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 250-52

[124] David Crystal (Editor), (1994), *The Cambridge Encyclopedia,* p.515

[125] *Ibid*, p 401

## 6.3. አካባቢያዊ፣ የባለሙያና የስሚ ስሚ ማስረጃ በኢትዮጵያ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ ጉዳይ[126] ስለቀጥተኛና አካባቢያዊ እንዲሁም የባለሙያ ምስክርነት ትናታኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፤ ንብረትነቱ የ1ኛና 2ኛ ተከሳሾች የሆነ መኪና በ3ኛ ተከሳሽ አማካኝነት ሲሽከረከር በፈጸመው ጥፋት ሠሌዳ ቁጥሩ አ.አ. 3-15306 በሆነ የአንበሳ አውቶቡስ ላይ ጉዳት በማድረሱ ካሳ እንዲከፈል ክስ በመቅረቡ ነው፡፡ 2ኛና 3ኛ ተከሳሾችም አደጋው የደረሰው በ3ኛ ተከሳሽ ጥፋት ሳይሆን የከሳሽን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር በፈጸመው ጥፋት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ለኛ ካሳ እንዲከፍለን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በመመርመር ከሳሽ ያቀረበው የፖሊስ ምርመራ መዝገብ በአደጋው ቦታ በተነሳው ፕላን መሠረት ጥፋቱ የ3ኛ ተከሳሽ መሆኑን እንደሚያስረዳ፤ በሌላ በኩል ግን ተከሳሾች ያሰሟቸው ምስክሮች አደጋው የደረሰው የተከሳሾች መኪና በቆመበት የከሳሽ መኪና መጥቶ በመግጨቱ መሆኑን በቦታው ስለነበሩ በዓይናቸው ማየታቸውን መስክረዋል፡፡ በመቀጠልም የከሳሽ ማስረጃ የሆነው የፖሊስ ምርመራ ሪፖርት ከአደጋው በኂላ ከነበረው ሁኔታ በመነሳት የተዘጋጀ በመሆኑና የተከሳሾች ማስረጃ ግን በቦታው የነበሩ ሰዎች ቃል ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሳሾች ማስረጃ ላይ የበለጠ እምነት በመጣል አደጋው የደረሰው የከሳሽን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሾፌር ጥፋት ነው በማለት ለተከሳሾች ካሳ እንዲከፈል ወሰነ፡፡ ከሳሽ (አንበሳ ኦቶቡስ) በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ውሳኔውን አፅንቶታል፡፡

በመጨረሻም የሰበር አቤቱታ ቀርቦ ጉዳዩ የተመረመረ ሲሆን ችሎቱ የማስረጃ ዓይነቶችን እንደሚከተለው መርምሯል፣

> በማስረጃ ዓይነቶች ክፍፍል የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ሊቀር[ቡ] የሚችሉት ማስረጃዎች ቀጥተኛ ማስረጃ (direct evidence) ወይም የአካባቢ ማስረጃዎች (circumstantial evidence) ተብለው ሊመደቡ የሚችሉ ሲሆን ምስክሮች በስሜት ሕዋሳቸው አማካኝነት የተፈለገው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖሩ(ን) እናውቃለን በማለት የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ቀጥተኛ ማስረጃ ተብሎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአካባቢ ማስረጃ የሌሎች [ኩነቶችን] መኖር አለመኖር በተዘዋዋሪ መንገድ ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ እንደሆነ በመስኩ ከዳበረው ሥነሕግ (jurisprudence) መገንዘብ ይቻላል፡፡[127]

አመልካች ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው የባለሙያ ሪፖርት ማለትም የኤክስፐርት ማስረጃ መሆኑን ችሎቱ በመመርመር፣

> አንድ ኤክስፐርት የሚሰጠው ቃል በፍ/ቤት እንዲረጋገጥ የተፈለገውን ጉዳይ በቀጥታ አይቻለሁ ወይንም ጉዳዩ በቀጥታ ሊረጋገጥ የሚችልበት በማንኛውም የስሜት አካሎች አማካይነት ተረድቻለሁ በማለት ሳይሆን በሙያው ሊረጋገጡ የሚችሉትን [ኩነቶች] ተመራምሮ ውጤቱን ወይም ግኝቱን የሚገልጽ ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃ በአካባቢ ማስረጃ ሥር ሊመደብ እንደሚችል ከዳበረው ሥነ-ሕግ መረዳት ይቻላል፡፡ የኤክስፐርት ማስረጃም ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ይህን ማስረጃ ሳይጠረጥረው ባለበት ሁኔታ የሚቀበለው ሳይሆን እንደማንኛውም ማስረጃ የሚመዘን (ነው)፣

የሚል ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም ከሳሽ ያቀረበው የፖሊስ ምርመራ የኤክስፐርት ማስረጃ ቢሆንም ብቃቱ የሚወሰነው በባለሙያው የእውቀት አድማስ፣ ከሚታገዝበት መሣሪያና በመሳሰሉት በመሆኑ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ማስረጃ (conclusive evidence) እንደማይሆንና በዓይን ምስክሮች የተነገረውን ኩነት የማስተባበል አቅም እንደሌለው፣እንዲሁም

[126] አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት v. እነ ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች፣ 2004 ዓ.ም፣ ቅጽ 12፣ ገጽ 388

[127] ዝኒከማሁ ገጽ 389

የኤክስፐርት ማስረጃ አካባቢያዊ ማስረጃ ስለሆነ ከቀጥተኛ ማስረጃ ጋር በተጻረረ ጊዜ የበለጠ ክብደት የሚሰጠው ለቀጥተኛ ማስረጃው መሆኑን በመግለጽ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በቀጥተኛ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ የሰጠው ውሳኔ ከማስረጃ አቀራረብ መሠረታዊ መርህ አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡[128] ይህ ውሳኔ ከላይ የተመለከትናቸውን ቀጥተኛ ማስረጃ፣ አካባቢያዊ ማስረጃና የባለሙያ ማስረጃ የሚመለከት ነው፡፡

## 6.4. በስሚ ስሚ ማስረጃ ላይ በኢትዮጵያ ያሉ ሕጎች[129]

‹‹የስሚ ስሚ›› የሚለው ቃል ‹‹ ሰማዒ›› ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ‹‹ሰማዒ›› ማለት ደግሞ የሚሰማ ፣ የሚቀበል፣ ‹‹ሰሚ መስካሪ፣..[130] ማለት ነው፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ ስንልም ቀደም ሲል የተመለከትነውን ትርጓሜ የሚይዝ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔርና ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት ሕጎች መሠረት ማናቸውም ምስክር በቀጥታና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ስለሚያውቀው ኩነት ወይም ድርጊት መመስከር ይችላል፡፡[131] እዚህ ላይ ‹ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ› የሚለው ሀረግ የስሚ ስሚ ማስረጃን ያካትታል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ አግባብነት አለው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሕግ ባለሙያዎች የሚሰጡትን ምላሽ በሁለት[132] መመደብ ይቻላል፡፡ ሀረጉ የስሚ ስሚ ማስረጃን አያካትትም የሚሉት ወገኖች ‹ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቀውን› የሚለው ሀረግ ምስክሩ ፍርድ ቤት በመገኘት ስለአንድ ነገር አስተያየት እንዲሰጥ የሚደረገውን ሁኔታ የሚያመለክት እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ በእነዚህ ባለሙያዎች አመለካከት መሠረት የምስክሩ ተግባር ስለኩነቱ መኖር አለመኖር መመስከር ሳይሆን በተሰጠው ኩነት ላይ አስተያየቱን መሠንዘር ነው፡፡ በመሆኑም ምስክሩ የሚመሰክረው እርሱ ስለተመለከተው፣ በቀጥታ ዕውቀት ስላገኘበት ጉዳይ ሳይሆን ከሌሎች ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስላገኘው ዕውቀት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የባለሙያ ምስክሮችን ብቻ የሚመለከት መሆኑ መጤን አለበት፡፡

ከላይ በተመለከትነው አንድ የመኪና ሞተር ጥገናን በሚመለከት በተነሳ ክርክር[133] ባለሙያዎች የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ባለሙያዎች አስተያየት የሰጡት የመኪናውን ሞተር የጠረበውን ወይም የፈታውንና የገጠመውን ሰው በመጠየቅ ካገኙትና ከሰሙት ተነስተው ነው፡፡ ይህን ማስረጃ በሚመለከት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የባሙያዎቹ አስተያየት የሚነቀፍ መሆኑን ሲተች፦

> … (ባለሙያዎቹ) የሰሟቸውን ሰዎች ቃል መሠረት አድርገው የሰጡት አስተያየት ትክክለኛ የሚሆነው የምስክሮች ቃል ትክክለኛ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አዋቂዎቹ የሰጡት አስተያየት ባዩትና በሚያውቁት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በሰሙትና ትክክለኛነቱ ባልተረጋገጠ የሦስተኛ ወገኖች ቃል ላይ ነው፡፡ ይህም አስተያየቱን የልዩ አዋቂ የሙያ ውጤት ሳይሆን ወደ ይመስላል ያዘነበለ የስሚ ስሚ (hearsay) ማስረጃ ውጤት ያደርገዋል፡፡

---

[128] ዝኒ ከማሁ ገጽ 390፡፡ የሰበር ችሎቱ ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የተደነገገ ሕግን ሳይሆን መሠረታዊ የማስረጃ ሕግ መርህን መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[129] በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ በኮመን ሎው የማስረጃ መርህ ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ረቂቅ ሕጎች ተዘጋጅተው የነበሩ ሲሆን መንግሥት ያለውን የማስረጃ ሁኔታ መከተሉን በመምረጥ ይመስላል ረቂቆቹ እንዳይጸድቁ አድርጓል፡፡

[130] ኪዳነወልድ ክፍሌ፣ 1948 *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ* 871

[131] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 263/1/እና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 137

[132] Menlik, *supra* note 81, p. 17

[133] ኩልማኒት አድሪያኖ *v.* ገብረ መድህን በኩረ፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 201/77፤ የፍርዶች መጽሐፍ፣ (1986 ዓ.ም.)

በማለት ማስረጃውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህ ውሳኔ የምንገነዘበው ቁም ነገር የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት የሌለው መሆኑን ነው፡፡

ስለጉዳዩ በቀጥታ ያልተገኘ ዕውቀት የስሚ ስሚ ማስረጃን አይጨምርም የሚል ክርክር ያለ ሲሆን ከፍርድ ቤቶቻችንም ከፊሎቹ ይህን አስተሳሰብ እንደሚቀበሉት ከውሳኔዎቻቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ሌሎች ባለሙያዎች ግን ሕጋችን የስሚ ስሚ ማስረጃን ቅቡልነት አይከለክልም በማለት ይከራከራሉ፡፡ ዳኞች ይህንኑ ክርክር በመቀበል ውሳኔ ሲሰጡ ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በአንድ የግድያ ወንጀል[134] ላይ ምስክሮቹ ተከሳሹ ያጠቃው መሆኑን ሟች ትናንት ነግሮናል በማለት የሰጡት የምስክርነት ማስረጃ ቅቡልነትን አግኝቷል፡፡ ከዚህም ሌላ ሟቹ በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እንዲሁ ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡

በሥነ-ሥርዓት ሕጎች የአማርኛ ቅጂዎች ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው በቀጥታ ያልተገኘ ዕውቀት ምስክሩ ‹‹ቀጥታ ባልሆነ መንገድ›› የሚያውቀው ወይም ሊያውቀው የሚችለው ነው፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው ይህ አባባል ‹ቀጥታ ያልሆነ እውቀት› ከሚለው የተለየ ሀሳብን ያዘለ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ በአማርኛው ቅጂ የሀረጉ አቀማመጥ ሰፊ በመሆኑ የስሚ ስሚ ማስረጃን ያካትታል፡፡[135] የረጅም ጊዜ የማስረጃ ሕግ የማስተማር ልምድ ያላቸው የሕግ ምሁር[136] እንደሚሉት ምንም እንኳ በፍርድ ቤቶች ዘንድ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነትን የሚያጣበት ጊዜ ቢኖርም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 263(1) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ቁጥር 137(1) ሥር ተካትቶ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የሥነ-ሥርዓት ሕጎች መሠረት የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት አለው ማለት ይቻላል፤ ይህም ከ‹‹ኮመን ሎው›› የሕግ ሥርዓት ያፈነገጠ ‹‹ከሲቪል ሎው› የህግ ሥርዓት መርህ ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ባለው በፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 እንደተደነገገው የስሚ ስሚ ወይም በተዘዋዋሪ የተገኙ ማስረጃዎች ቅቡልነት ያላቸው ማስረጃዎች ናቸው፡፡[137] ይህ አዋጅ በግልጽ እንደደነገገው የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ግን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን ይቃረናል፡፡ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት ሕገመንግሥታዊ መብት ስለመሆኑ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመረመረው አንድ የወንጀል ጉዳይ የስሚ ስሚ ማስረጃን የሚያካትት ነው፡፡ በጉዳዩ ተጠሪ የሆነው አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የተመሠረተበት ሲሆን፣ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩን ለማስረዳት ተበዳይ ራስዋን፣ እና ስለጉዳዩ የሰሙ ሌሎች ምስክሮችን ፍ/ቤት አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ሆኖም ግን የከፍተኛው ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን ላይ ይግባኝና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎት ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንተውታል፡፡ ከዚያም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቀርቦ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡

የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን እንደመረመረው ዐቃቤ ሕግ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ ለማስረዳት ያቀረበውና ያሰማው ማስረጃ የግል ተበዳይን፣ አምስት ምስክሮችንና የሀኪም (የጽሁፍ) ማስረጃን ያካትታል፡፡ በዚህም መሠረት ተበዳይዋ በሰጠችው የምስክርነት ቃል ዐቃቤ ሕግ በክሱ በጠቀሰው ቀንና ሰዓት ተበዳይ ቡና ስታፈላ ከነበረችበት ክፍል ውሃ አቀብይኝ ብሎ ተጠሪው እንደጠየቃትና ውሃ ስትወስድለት ከራሱ ቤት በር ሥር ቆሞ እንደጠበቃት፣ ይዟት ወደ መኝታ

[134] ዐቃቤ ሕግ v. ምህረት ተሾመ የአዲስ አበባ ከፍተኛው ፍ/ቤት የወ/መ/ቁጥር 306/81 ያልታተመ

[135] Menlik, *supra* note 81, p. 17

[136] Daniel Haile, (1994), *Lecture Note on Law of Evidence*, Addis Ababa University, Faculty of Law.

[137] አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ.ም የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ፤ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣* አስራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር 57፤ አዲስ አበባ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም፤ አንቀጽ 23(2)

ክፍሉ በመውሰድ አስገድዶ እንደደፈራት፣ እርሷም በጊዜው ራሷን ስታ እንደነበር፣ ሰውነቷ እንደደማ፣ ከዚያም ጩኸት እያሰማች 3ኛና 4ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን መጥራቷን፣ ተጠሪም ቀስ አድርጎ በማስኬድ ወደ ቤቷ እንዳስገባት ስለመመስከሯ በከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገብ ላይ ሠፍሯል፡፡

2ኛዋ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተጠሪ የግል ተበዳይዋን ሲደፍር አለማየቷን በመግለጽ በክሱ በሰፈረው ቀንና ሰዓት የግል ተበዳይ ቡና ስታፈላላቸው ቆይታ ከአቦል በኋላ ያለውን አፍልታ ለማምጣት ወደ ኩሽና ቤት መውጣቷን፣ ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ ተጠሪ ድንግልናየን ወሰደብኝ እያለች እየጮኸች መምጣቷን፣ ልብሷን ወደላይ አድርጋ ስታያትም ደም ማየቷን፣ የግል ተበዳይን ይዛ ወደ ተጠሪው ቤት ስትሄድ ተጠሪው እቤቱ ውስጥ ሆኖ ቆዩ ሰው እየመጣ ነው ሲል ስለመስማቷ መመስከሯን መዝገቡ እንደሚያመለክት የሰበር ሰሚው ውሳኔ ያትታል፡፡ 3ኛ እና 4ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም በክሱ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ገደማ በተጠሪው ቤት ተቀምጠው ሳለ የግል ተበዳይ የተጠሪን ቤት ማንኳኳትዋን፣ እነርሱም በሩን ከፍተው ሲወጡ ተጠሪ አስገድዶ ስለደፈረኝ ጠይቁልኝ ማለቷንና እነርሱም እናነጋግርልሻለን በማለት መልስ እንደሰጧት መዝገቡ ያመለክታል፡፡ 5ኛው ምስክር ፖሊስ ሲሆን የግል ተበዳይዋ በተባለው ቀን ማግስት መደፈሯን በመግለጽ ስለማመልከቷ፣ ተጠሪም እንዳመለከተች እንደጠየቀውና ወደፊትም ክሱ የሚደርስበትን ደረጃ ትነግረኛለህ እንዳለው መስክሯል፡፡ ከነዚህ ምስክሮች በተጨማሪ ከግምቢ ሆስፒታል የተሰጠ የሀኪም ማረጋገጫም በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ የሰበር ችሎቱም ስለማስረጃዎቹ ሲተነትን፣

> … ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃዎች በዝርዝር ይዘታቸውም ሆነ በጊዜ እና ሰዓት አጠቃቀስ ረገድ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ ሲጠቃለሉም በጊዜው ተፈጸመ የተባለውን ድርጊት በሚገባ መፈጸሙን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ አንድ ክስን የሚሰማ ፍ/ቤት በክሱ አከራካሪ የሆኑትን [ኩነቶች] እውነት መሆን አለመሆን … ማረጋገጥ የሚቻለው በሚቀርብለት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በእርግጥም የማስረጃውን ይዘት በመመርመር ክብደቱንና ቅለቱን የመመዘን ሥልጣኑም የፍ/ቤት ነው፡፡ ይሁንና ማስረጃውን በግልጽ ከመዝገቡ እና ይዘቱም ምን እንደሚመስል እያየ ግን ማስረጃ እንዳልቀረበ አድርጎ ማለፍ ይችል ዘንድ ሕግ አይፈቅድለትም፡፡ የአንድ አከራካሪ [ኩነት] እውነት … የሚረጋገጠው በማስረጃ ነው የሚለውን መርህም መጣስ አይችልም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ዐቃቤ ሕግ ያሰማው ማስረጃ በሕጉ የተደነገገው ወንጀል ስለመፈጸሙ በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ይህን የመሰለውን ማስረጃ እንዳላዩ አድርገው አልፈውታል፡፡ በእኛ ግንዛቤ እና እምነት ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሕግን በግልጽ የጣሰ ብቻ ሳይሆን፣ ፍትሕንም በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡…

ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ የትኛው ሕግ ላይ መሠረታዊ ስህተት እንደተፈጸመ የሰበር ችሎቱ አልገለጸም፡፡ ከመዝገቡ እንደምንረዳው በተለይ ከግል ተበዳይዋ ውጭ ያሉት ምስክሮች የስሚ ስሚ ምስክሮች ናቸው፡፡ ከሰበር ችሎቱ ውሳኔ የምንገነዘበው የስሚስሚ ማስረጃ[138] እውነትን የሚያረጋግጥ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ቅቡልነት ያለው ማስረጃ መሆኑን ነው፡፡ ከጉዳዩም እንደምንገነዘበው የግል ተበዳይም በፍ/ቤት ቀርባ መስክራለች፡፡ ይህ የማስረጃውን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ ዕድል ይሰጣል፡፡

የስሚ ስሚ ማስረጃ ፍትሐብሔር ጉዳይ ቅቡልነት ያለው ሲሆን በወንጀል ጉዳይም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 137(1) መሠረት ተቀባይነት አለው፡፡ ሆኖም የበላይ ሕግ በሆነው ሕገመንግሥት አንቀፅ 20(4) መሠረት የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት እንደሌለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የስሚ ስሚ ማስረጃ የተከራካሪን ወገን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ ዕድል

[138] የሰበር ችሎቱ የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ሲል የስሚስሚ ማስረጃንም የሚያጠቃልል ነው፡፡ ለዝርዝሩ ጉዳዩን ገጽ 81 ላይ ይመልከቱ፡፡

ስለሚያጠብ አሊያም ስለሚያሳጣ ማስረጃን የመጋፈጥ ሕገመንግሥታዊ መብትን ይቃረናል፡፡ ስለሆነም፡ በወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረ ሰው ያለአግባብ እንዳይወሰንበት ሕገመንግሥታዊ መብቱን ለማስከበር የስሚ ስሚ ማስረጃን በወንጀል ጉዳይ አለመቀበሉ የተሻለ መሆኑን ፀሐፊው ያምንበታል፡፡

## ማጠቃለያ

የስሚ ስሚ ማስረጃ በ‹ኮመን ሎው› የሕግ ሥርዓት የተለያየ ትርጉም እንደሚሰጠው ተመልክተናል፡፡ ሰፊ ትርጓሜውን ስንመለከት፣ የስሚ ስሚ ማስረጃ ማለት ፍርድ ቤት ችሎት ያልቀረበ ሰው አስቦበትም ሆነ ከቁጥጥሩ ውጭ በሆነ ሁኔታ በምርመራ ላይ ስላለው ኩነት እውነትነት ወይም ሀሰትነት የገለጸውን ሌላው ሰው ፍርድ ቤት በመቅረብ በቃል፣ በጽሑፍ፣ ወይም ቃል አልባ በሆነ ድርጊት የሚሰጠው ማረጋገጫ ነው፡፡ አንድ ምስክር ራሱ ስለሰማው፣ ስላሸተተው ወ.ዘ.ተ ጉዳይ ሊመሰክር ይችላል፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ ግን ምስክሩ የሚመሰክረው ራሱ በቀጥታ ስለተመለከተው፣ ስለሰማው፣ ስላሸተተው ወ.ዘ.ተ ጉዳይ ሳይሆን ፍርድ ቤት ያልቀረበ ሌላ ሰው የነገረውን ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የስሚ ስሚ ምስክርነት ብቃት በዋነኛነት የሚመሠረተው ፍርድ ቤት ባልቀረበው ሰው ብቃት ላይ ነው፡፡ የስሚ ስሚ ማስረጃ ከአካባቢዊ ማስረጃ የተለየ ሲሆን ከባለሙያ ማስረጃ ጋርም ፍፁም ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል፡፡

በ'ኮመን ሎው' የሕግ ሥርዓት የስሚ ስሚ ማስረጃን የሚመለከት ደንብ ያለ ሲሆን በመርህ ደረጃ የስሚ ስሚ ማስረጃ ቅቡልነት የሌለው ማስረጃ ነው፡፡ ምክንያቱም የስሚ ስሚ ማስረጃ ዋናው ተናጋሪ መግለጫውን የሚሰጠው ከፍ/ቤት ውጭ በመሆኑ ሲናገር በማየት እውነት ስለመናገሩ ማረጋገጥ ስለማይቻል፣ መግለጫው በመሃላ ያልተረጋገጠና መስቀለኛ ጥያቄ የማይቀርብበት በመሆኑና ምስክሩን መመርመር ስለማይቻል እውነተኛነቱ አጠራጣሪ በመሆኑና የማይታመን በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም፣ በልዩ ደንቡ መሠረት ማስረጃው ተዓማኒ ከሆነ፣ ቀጥተኛ ምስክርነት የሚሰጠው ሰው ፍ/ቤት ቀርቦ ለመመስከር የማይገኝ ከሆነ፣ እንዲሁም ማስረጃው ለጉዳዩ አግባብነት ካለው በማስረጃነት ቅቡልነት አለው፡፡ በ'ሲቪል ሎው' የሕግ ሥርዓት ግን የስሚ ስሚ ደንብ (Rules of Evidence) ስለሌለ የስሚ ስሚ ማስረጃ በመርህ ደረጃ ቅቡልነት አለው፡፡

በኢትዮጵያ የስሚ ስሚ ማስረጃን በሚመለከት ሁለት የተለያዩ አቋሞች ያሉ ሲሆን፣ ይህ ችግር ከሕጎች የግልጽነትና የመስተጋብር ክፍተት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገመንግሥት አንቀጽ 20(4) መሠረት የወንጀል ተከሳሾች የቀረቡባቸውን ማስረጃዎች የመጋፈጥና የመመርመር መብት ያላቸው ሲሆን፤ የወንጀል ፖሊሲውም በተከሳሽ ላይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች በሙሉ ለተከሳሹ ቀርበው መመርመር እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሠረት ሕጎቻችን ሊስተካከሉ ይገባል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የወንጀል ሕጎች ለሰብአዊ መብት ጥበቃ እየሰጡ በመሆኑ በተቻለ መጠን የተከሳሾችን ሕገመንግሥታዊ መብቶች ለማስጠበቅ ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ስለሆነም በመርህ ደረጃ የስሚ ስሚ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ ቅቡልነት እንዳይኖረው ተደርጎ፣ ተከሳሽ የቀረበበትን ማስረጃ ለመመርመር ያለው መብት ሳይጣስ (ተናጋሪው የማይገኝ ሲሆን እንዲሁም ማስረጃው ተኣማኒ ሆኖ ሲገኝ) በልዩ ሁኔታ ብቻ (as an exception) የስሚ ስሚ ቅቡልነት እንዲኖረው መደንገግ አለበት፡፡ ይህም በአንድ በኩል የተከሳሾች መብት እንዲጠበቅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በቀጥተኛ ማስረጃ እጦት ምክንያት አጥፊዎች ከተጠያቂነትና ከቅጣት እንዳያመልጡ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ■